# እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ

## የስደተኞች መመሪያ



Amharic

# እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ

## የስደተኞች መመሪያ

ሁለተኛ እትም
2003

በባህል ማስተዋወቂያና ኢንፎርሜሽን ማዕከል የተዘጋጀ

ይህ መፅሀፍ የታተመው፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት ማለትም በስቴት ዲፓርትመንት ስር ከሚገኘው የህዝብ የስደትና ስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር ነው። ይሁንና መፅሀፉ የስቴት ዲፓርትመንት ኦፊሴላዊ ሰነድ አይደለም።

መፅሀፉን እንዳለ ማባዛት ይቻላል። ዳሩ ግን በውስጡ ያሉትን ፎቶግራፎችና ጥቅሶች፣ ያለ ለጋሽ ድርጅቶች ፈቃድና ስምምነት በሌሎች ህትመቶች ላይ ማውጣት ወይንም ለሌላ አላማ መጠቀም አይቻልም።

ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘረው ድርጅቶችና የተቋማት ወኪሎች እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ፣ የስደተኞች መመሪያ ለተሰኘው መፅሀፍ ዝግጅት፣ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በኒው ዮርክ የአፍሪካውያን አገልግሎት ኮሚቴ
የባህል ማስተዋወቂያና የኢንፎርሜሽን ማዕከል
የአለም አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት
አለም አቀፍ የካቶሊክ ስደት ኮሚሽን
በፔንሲልቬኒያ አለም አቀፍ የኤሪ ተቋም
አለም አቀፍ የስደት ድርጅት IOM
አለም አቀፍ የመድህን ኮሚቴ
የአዮዋ የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል
በቦልቲሞር የአይሁድ ቤተሰብ አገልግሎት
በናሽናል ካፒቶል አካባቢ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎት
በሰሜን ዳኮታ የፋርጎ ሉተራን ማህበራዊ አልግሎት
በሜሪላንድ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ
የስደተኞች ማቋቋሚያ ቢሮ
በሂውስተን የስደተኞች አገልግሎት ጥምረት
የዩናይትድ ስቴትስ ካቶሊክ ጉባኤ
የአለም ስደተኞች መርጃ አገልግሎት

ፎቶግራፎችና ጥቅሶች የለገሱት ቀጥሎ ተዘርዝረዋል

ፎቶግራፎች፣

የአሪዞና አለም አቀፍ የስደተኞች ኮንሶርቲየም
የስነ ቋንቋዎች ማዕከል
በኖርዝ ዳኮታ የፋርጎ ሉተራን ማህበራዊ አገልግሎት
ናሽናል ካፒቶል አካባቢ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎት
ፎቶ ዴስክ ኢንኮርፖሬትድ

ጥቅሶች፣
ስካተርድ ችልድረን (የህፃናት አድን የስደተኞች ፕሮግራም)
በዩናይትድ ስቴትስ የቦዝኒያ ስደተኞች ማቋቋሚያ፣ ክፍል 2
የስደተኞች ምላሽ (የስነ ቋንቋዎች ማዕከል)

ሽፋንና ዲዛይን፣ ሳጋርት ዲዛይን SAGART DESIGN

እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ፣ የስደተኞች መመሪያ የተሰኘው መፅሀፍ፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጥተው ገና በመቋቋም ላይ የሚገኙ ስደተኞች፣ በመጀመሪያዎቹ ወራት ቆይታቸው ምን እንደሚያጋጥማቸውና ምን አይነት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጓቸው አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል።

መፅሀፉ፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚመጡ ስደተኞች ስለ ስራ፣ ትምህርት፣ ጤናና አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታዎች ሊኖራቸው የሚገባውን አስተሳሰብ ከተጨባጭ እውነታ የራቀ እንዳይሆን ግንዛቤ ያስጨብጣል።

የመመሪያ መፅሀፉ የተዘጋጀው፣ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት የህዝብ ስደትና ስደተኞች ቢሮ በሰጠው መመሪያ መሰረት ነው። የፌደራልና የስቴት የማቋቋሚያ ድርጅቶች ወኪሎችና በቅርቡ ተቋቁመው ራሳቸውን የቻሉ ስደተኞች፣ ለመፅሀፉ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

መፅሀፉ በበርካታ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለሚመለከታቸው ጉዳይ አስፈፃሚ ድርጅቶችና ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው በውጪ ሀገሮች እየተጠባበቁ ላሉ ስደተኞች ይታደላል። አዲስ ስደተኞችን ለማቋቋም የሚረዱ ድርጅቶችም፣ ስደተኞች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመግባታቸው በፊት ስለ አሜሪካ ምን ያህል መረጃ ማግኘታቸውን እንዲረዱ መፅሀፉ ይሰጣቸዋል።

እንኳን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በደህና መጡ፣ የስደተኞች መመሪያ ከዚህ ቀደም የነበረውንና በዩናይትድ ስቴትስ የመቋቋሚያ መመሪያ የተሰኘውን መፅሀፍ ተክቶ የሚያገለግል ይሆናል።

# ማውጫ

ማገናዘቢያ 3

መግቢያ 5

የቅድመ መዳረሻ ሂደት 9

የማቋቋሚያ ድርጅቶች ሚና 17

የኮሚዩኒቲ አገልግሎቶች 21

መኖሪያ ቤት 27

መጓጓዣ 33

ስራ 37

ትምህርት 53

ጤና 63

የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም 69

የስደተኛ መብቶችና ሀላፊነት 75

አዲስ ባህል መልመድ 81



ይህ የመቋቋሚያ መመሪያ መፅሀፍ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ራስዎን እንዲያዘጋጁ ይረዳዎታል። ራስዎን የሚያቋቁሙባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ምን እንደሚመስሉ ከመግለፁም በላይ፣ ስለ መሰረታዊ የአሜሪካ የኑሮ ሁኔታዎች መረጃ ይሰጣል። ምንም አይነት ማስተዋወቂያና መመሪያ፣ ማወቅ የሚገባዎትን ነገር ሁሉ ሊያሳውቅዎ አይችልም። ምክኒያቱም ስደትና መልሶ መቋቋም ረጅምና ውስብስብ ሂደት በመሆኑ፣ እያንዳንዱን ስደተኛ የሚገጥሙት ሁኔታዎች ተመሳሳይ አይሆኑም። በመፅሀፉ ላይ ከተዘረዘሩት ነገሮች ውስጥ ያልገባዎ ካለ፣ ወይንም ደግሞ ስለ አሜሪካ የኑሮ ሁኔታ ላለዎት ጥያቄ መፅሀፉ ምላሽ ካልሰጠ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከደረሱ በኋላ የሚያቋቁሞትን ድርጅት ሰራተኛ ጠይቀው፣ መልስ እንዲያገኙ ይረዳዎታል። ግልፅና የጠያቂነት ዝንባሌ ያለው አመለካከት ቢይዙ፣ ለዩናይትድ ስቴትስ ኑሮዎ የሚበጅና ለአዲሱ ህይወትዎ ስኬታማነት አጋዥ የሚሆን ጠቃሚ መንገድ ተከተሉ ማለት ነው።

መልካሙን እንመኝልዎታለን!







ዩናይትድ ስቴትስ ሰፊና የተለያዩ ነገሮችን ያቀፈች ሀገር ናት። ስለዚህም ስለ አሜሪካ ከአንድ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቸግራል። የተለያዩ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ጠባዮች ያሏትና ራሳቸውን አሜሪካውያን ብለው የሚጠሩ የተለያዩ ህዝቦች ያቀፈች ሀገር ናት። አሜሪካውያን የተለያየ የዘር ሀረግና ትውልድ ያላቸው ሲሆኑ የተለያዩ ሀይማኖቶች፣ እምነቶችና እሴቶችን ይከተላሉ። በመሆኑም ስለ አሜሪካ ከሰሙት መካከል አብዛኛው ከእውነታው የራቀ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። በዩናይትድ ስቴትስ ከቆዩ ጓደኞችዎ ወይንም ሌሎች ሰዎች ያገኙት ወይንም የሰሙት መረጃ እንኳን ቢሆን፣ በራስዎ ዓይን ሲታይ እውነት ላይሆን ይችላል።

እያንዳንዱ የዩናይትድ ስቴትስ ኮሚዩኒቲ ወይንም ህብረተሰብ በራሱ የተለየ እንደመሆኑ መጠን፣ ከአዲስ መጪዎች ጋር የሚኖረው አግባብም እንዲሁ የራሱን መንገድና ስርዓት ይከተላል። የሚያቋቁምዎ ድርጅት ሰራተኞች ስለ አዲሲቱ ሀገርዎና ስለሚቀላቀሉት ማህበረሰብ፣ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያረዱዎታል።

አንዱና በቶሎ የሚገነዘቡት ነገር የአብዛኞች አሜሪካውያን እምነት፣ ራስን በመቻልና በግል ሀላፊነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። ስራ መስራት እስከቻሉ ድረስ፣ ቶሎ ስራ ይዘው ራስዎንና ቤተሰብዎን እንዲያስተዳድሩ ይጠበቃሉ። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታዎ ውሱንና ደካማ መሆን፣ ስራ ከመስራት አያግዶትም። ይሁንና የተሻለ የስራ እድገትና ውጤት ለማግኘት፣ እንግሊዘኛን ቶሎ መማር ያስፈልጋል። አብዛኞቹ የኮሚዩኒቲ ድርጅቶች፣ ራስዎን ለማሻሻል የሚረዱ ትምህርቶች ይሰጣሉ።

ሁለተኛው የሚገነዘቡት ነገር፣ ስደትና መቋቋም ቋሚ ወይንም ዘላቂ ውሳኔ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ በዩናይትድ ስቴትስ ቋሚ ነዋሪ ብሎም ዜጋ ለመሆን የመጀመሪያ እርምጃ ነው።

ከአንድ አመት ቆይታ በኃላ በዩናይትድ ስቴትስ ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ከአራት ዓመት ተኩል በኃላ ደግሞ የአሜሪካ ዜግነት ለማግኘት የሚያመለክቱበት ህጋዊ ብቃት ያገኛሉ።

በስደተኛነትዎ የነበረዎትን ንብረት በሙሉ አጥተው ይሆናል። ይሁንና በዩናይትድ ስቴትስ ህይወትዎን እንደ አዲስ ለመጀመርና ለመገንባት ዕድል ያገኛሉ። አዲስ ኑሮን ሀ ብሎ መጀመር ቀላል አይሆንም፣ ዳሩ ግን ሊሆንና ሊከናወን ይችላል። ከእርስዎ በፊት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ስደተኞች ወደ አሜሪካ የመጡ ሲሆን አብዛኞቹ ኑሮ ተሳክቶላቸዋል። ወዲህ የመጡት የራስዎ የሆነ ልዩ ተሰጥዎ፣ ታሪክ፣ ባህል እንዲሁም ጠንካራ ስብዕናና ወኔ ይዘው በመሆኑ ኑሮዎን ሊያሳኩ ይችላሉ።


ከእርስዎ ቀድመው የመጡ ስደተኞች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በጎ ምክሮች ሊያካፍልዎ ይችላሉ፤

- ምን ጊዜም ነፃና ክፍት አመለካከት ይኑርዎ
- ከድምዳሜ ለመድረስ አይቸኩሉ
- የእንግሊዘኛ ቋንቋን ለመማርና ለመናገር ይሞክሩ
- የአሜሪካን ባህል ሳይተቹና ከራስዎ ባህል ጋር ሳያነፃፅሩት ሊረዱት ይሞክሩ
- በአሜሪካ ኑሮ መሳተፍ ይሞክሩ
- ትኩረትዎ፣ ምን ያህል ቀረኝ ሳይሆን ምን ያህል ተጓዝኩ በሚለው ላይ ይሁን
- ፈጥነው ስራ ለመያዝና፣ ቀስ በቀስም የተሻለ ስራ ለማግኘት ያቅዱ

ቀጥለው የተዘረዘሩት ምዕራፎች፣ ለመቋቋም ሂደትዎ የሚጠቅሙና ስለ አዲሱ ኑሮዎም ሆነ ስለ አዲሲቱ አገርዎ መረጃዎች የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች እጥር ምጥን ብለው የተዘጋጁ በመሆናቸው ሁሉን ሊያሟሉ አይችሉም። ልብ ይበሉ፣ አሜሪካውያን በአብዛኛው ራስን መቻል የሚለውን መርህ መከተላቸው እውነት ቢሆንም፣ ጥያቄ የሚጠይቃቸውን ሰው ያከብራሉ ያደንቃሉም። ለማወቅና ለመማር ተመራጩ መንገድ ነው።




OIM
IOM







የዩናይትድ ስቴትስ የዜግነትና የኢሚግሬሽን አገልግሎት CIS ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲገቡ ፍቃድ ከሰጠዎት በኃላ፣ ወደ አሜሪካ ከመጓዝዎ በፊት ሊከናወኑ የሚገባቸው ጥቂት ጉዳዮች አሉ። እነዚህም፣

- እርስዎና ቤተሰብዎ የጤና ምርመራ ማድረግ አለባችሁ
- በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኝ የማቋቋሚያ ድርጅት፣ ከመምጣትዎ ቀደም ብሎ ዝግጅት ያደርጋል
- ቅድመ ዝግጅቶቹ በሙሉ ከተጠናቀቁ በኃላ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚያደርጉት ጉዞ ይታቀዳል

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመምጣት በመጠባበቅ ላይ ሳሉ፣ ሂደቱን የሚከታተለው ወገን፣ ለጤና ምርመራዎ ቀጠሮ መያዙንና የሚያቋቁምዎ ድርጅት ስለ እርሶና ስለቤተሰብዎ በቂ መረጃ ማግኘቱን ያረጋግጣል። ከዛም የዩናይትድ ስቴትስ ጉዞዎን ያመቻቻል። በጉዞዎ ወቅት ተሽከርካሪ ወንበር፣ ምርኩዝ ወይንም ሌላ አይነት እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ለጉዞ አስፈፃሚ ወኪልዎ አስቀድመው ያሳውቁ። ጉዞዎን ለማከናወን በሚጠባበቁበት ወቅት፣ በተቻለዎ መጠን ስለ ዩናይትድ ስቴትስ ለማወቅና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ለመማር መሞከሩ ይጠቅማል።



## የጤና ምርመራ

እርስዎና ቤተሰብዎ የጤና ምርመራ ማድረግ ይጠበቅባችኋል። በበርካታ ስፍራዎች ይህ አገልግሎት በነፃ ይሰጣል። የጤና ምርመራው፣

- ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመምጣትዎ በፊት፣ መታከም የሚችሉ የጤና ችግሮች ያለዎት ከሆነ ለማወቅ ይረዳል
- እርሶም ሆኑ ቤተሰብዎ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዳይጓዙ የሚያግዱ የጤና ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል
- እርስዎና ቤተሰብዎ ዩናይትድ ስቴትስ ከደረሳችሁ በኃላ፣ ቀጣይ የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ላሉ የማቋቋሚያ ድርጅቶች መረጃ ይሰጣል

የጤና ምርመራ አድርገው በአንድ አመት ውስጥ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ካልተጓዙ፣ ሌላ የጤና ምርመራ ማድረግ አለብዎት።



## ከጉዞ በፊት የሚደረግ ቃለ መጠይቅ


የመቋቋም ሂደትዎ የተቃና እንዲሆን የሚያግዝ መረጃ ለማግኘት፣ አስፈፃሚው ወኪል ቃለ መጠይቅ ያደርግሎታል። በዩናይትድ ስቴትስ ዘመድ ወይንም ጓደኛ ካለዎት ስም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። የቤተሰብዎ አባል ማለት ባለቤትዎ ወይንም ልጆችዎ በዩናይትድ ስቴትስ ካሉ፣ እነሱ በሚኖሩበት ከተማ እንዲመደቡ ይደረጋል። በዩናይትድ ስቴትስ ያለ የሩቅ ዘመድዎ ወይንም ጓደኛዎ ባሉበት ስፍራ መመደብ ቢፈልጉ፣ የማቋቋሚያው ድርጅት በጠየቁት ስፍራ አስፈላጊ አገልግሎቶች መኖራቸውንና የስራ እድልን ከግምት በማስገባት፣ ውሳኔ ይሰጣል። ወደ አሜሪካ ከሚጓዙ ዘመዶችዎ ጋር አብረው በአንድ አካባቢ ለመስፈር ቢፈልጉ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፣ ዳሩ ግን ለመሳካቱ ማረጋገጫ መስጠት አይቻልም።



የሚሰፍሩበትን ስፍራ በተመለከተ የሚያቋቁምዎ ድርጅት ጥሩ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ፣ ከጉዞዎ በፊት ለአስፈፃሚው ወኪል ትክክለኛ መረጃ መስጠትዎን ያረጋግጡ። ምክኒያቱን አንዴ ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡ በኃላ ወዲያው የሚኖሩበትን ስፍራ ለመቀየር ያዳግታልና። ከዚህ በተጨማሪም አብዛኞቹ የማቋቋሚያ ድርጅቶች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚገኙት፣ ስደተኞች እንዲሰፍሩ በሚደረጉባቸው አካባቢዎች ብቻ ነው።

## የማቋቋሚያ ድርጅቶች

ዩናይትድ ስቴትስ እንደገቡ በመጀመሪያዎቹ ወራት፣ ከአሜሪካ የማቋቋሚያ ድርጅቶች አንዱ እንዲረዳዎት ይመደባል። ይህ ድርጅት ስለ እርስዎና ስለ ቤተሰብዎ አጠቃላይ መረጃ ይደርሰዋል። መረጃው የእርስዎንና የቤተሰብዎን ስም፣ እድሜ፣ ሙያ፣ ሀገር፣ ዘርና ሀይማኖት እንዲሁም ክትትል የሚያስፈልገው የጤና ችግርና በዩናይትድ ስቴስ የሚገኙ ዘመዶችዎን አድራሻ ያካትታል። የት ከተማ እንደሚሰፍሩ የሚወሰነው በማቋቋሚያው ድርጅት ይሆናል።



በዩናይትድ ስቴትስ ከቆዩ ቤተሰብዎ ወይንም ዘመዶችዎ ጋር መቀላቀል ያስፈልግ እንደሆነ፣ የስራ ዕድል መኖርና የአገልግሎቶች መገኘት ከግምት ውስጥ ይገባሉ። በዚህም መሰረት ከጉዞዎ በፊት የት እንደሚሰፍሩ ይነገረዎታል። ማቋቋሚያ ድርጅቱ፣ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ሲደርሱ የሚቀበልዎት ሰው፣ የሚያርፉበት ቤትና ስለሚኖሩበት ኮሚዩኒቲ መረጃ ማዘጋጀቱን ያረጋግጣል። (ስለ"ማቋቋሚያ ድርጅቶች ሚና" በገፅ 17 ላይ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።)

## ጉዞ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ

ጉዞዎን ራስዎ ሊያቅዱት ወይንም ደግሞ አስፈፃሚው ወኪል እንዲያቅዱልዎት ሊጠይቁ ይችላሉ። ራስዎ የሚያቅዱት ከሆነ፣ ገና ከመነሳትዎ በፊት ለአስፈፃሚው ወኪል ያስታውቁ።

ትኬት የሚገዛልዎት አስፈፃሚው ወኪል ከሆነ፣ ገንዘቡን የሚከፈል ብድር አድርገው ይቁጠሩት። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመምጣትዎ በፊትም የትኬትዎን ወጪ መልሰው የሚከፍሉ ለመሆንዎ ማረጋገጫ ይፈርማሉ።

ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡ በኋላ ከሶስት እስከ ስድስት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ፣ የጉዞዎን ወጪ በሶስት አመት ክፍያ እንዲሸፍኑ የሚያደርግ ወርሀዊ የክፍያ ማስታወሻ ማለት BILL ይላክልዎታል። በዚህ ሁኔታ የሚከፍሉት ገንዘብ፣ ሌሎች ተቋቋሚ ስደተኞችን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለማምጣት ይውላል።

እንደማንኛውም የአለም አቀፍ መንገደኛ ሁሉ፣ የእርስዎም ሆነ የቤተሰብዎ ሻንጣ ክብደትና መጠን ገደብ አለው። በበረራዎ ወቅት መከተል ስላለብዎት ደንብ አስፈፃሚውን ወኪል ይጠይቁ። የሻንጣዎ ክብደት ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ፣ ለሚመጣው ተጨማሪ ክፍያ ሀላፊው ራስዎ ይሆናሉ። ለትርፍ ኪሎ የሚጠየቀው ክፍያ እጅግ በጣም ውድ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ውሻና ድመት የመሳሰሉ የቤት እንስሳትን ይዘው መጓዝ ከፈለጉ፣ የማጓጓዣውን ወጪ መሸፈን እንዲሁም የዩናይትድ ስቴትስን የጉምሩክ ህግና የአየር መንገድ ደንብ መከተል ይጠበቅብዎታል። የቤት እንስሳትን ይዘው የሚጓዙ ከሆነ፣ ለአስፈፃሚው ወኪል በቅድሚያ ያሳውቁ። ምክኒያቱም ዩናይትድ ስቴትስ ሲደርሱ የሚቀበልዎት የማቋቋሚያ ድርጅት፣ ይህንኑ አውቆ የቤት እንስሳትን ማኖር የሚፈቀድበት መኖሪያ ቤት እንዲያዘጋጅልዎ ይረዳል።


የዩናይትድ ስቴትስ ጉምሩክ መስሪያ ቤት፣ ማንም ሰው ወደ አሜሪካ ይዞ እንዳይገባ የሚከለክላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። እነዚህም ናርኮቲክስ ማለት አደንዛዥ ዕፆች፣ ፍራፍሬዎች፣ ዕፅዋት፣ አትክልትና እርጥብ ስጋ ናቸው። በሀኪም የተፈቀደ መድሀኒት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ማስገባት ይቻላል። ይሁንና የመድሀኒቱ ምንነት በግልፅ ተለይቶ መቀመጥ አለበት። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መግባት የሚችሉና የማይችሉ ነገሮችን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት አስፈፃሚውን ወኪል ይጠይቁ።

ጉዞዎ በተለያዩ ትራንዚቶች የሚያሳልፍዎ ከሆነ፣ መተላለፊያ በሮች ላይ የአለም አቀፍ ስደተኞች ቢሮ የIOM ወኪሎች ይረዱዎታል።



በጉዞ ላይ ችግሮች ቢገጥምዎ ለምሳሌ የቤተሰብዎ አባል ቢታመም፣ የIOM ወኪሎች ይረዱዎታል። በችግር የተነሳ የመድረሻዎ ጊዜ የሚዘገይ ወይም የሚራዘም ከሆነ የIOM ተወካዮች ለሚያቋቁምዎት ድርጅት ያሳውቃሉ። ዩናይትድ ስቴትስ ሲደርሱም የIOM ተወካዮች በስፍራው ተገኝተው በኢሚግሬሽን ሂደት ይረዱዎታል። ጉዞዎ ቀጣይ ከሆነም ሌላ በረራ እንዲይዙ እገዛ ይሰጥዎታል።

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ጉዞ ከመጀርዎ በፊት ለመግቢያ የሚያስፈልግዎ ሰነዶች ያሉበት ጥቅል ወይንም ፖስታ ይሰጥዎታል። ጥቅሉ የኢሚግሬሽን፣ የጤናና የሰፈራ ሰነዶችን ይጠቀልላል። ሰነዶቹን ከእርስዎ ጋር ያስቀምጧቸው፣ በጉዞዎ ላይ እነዚህ ሰነዶች እንዳይጠፉብዎ ይጠንቀቁ፣ ጥቅሉን አይክፈቱ ወይንም ሻንጣዎ ውስጥ አይክተቱ። ዩናይትድ ስቴትስ በገቡበት በመጀመሪያው አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ፣ ጥቅሉን ለኢሚግሬሽን ባለስልጣናት ይስጡ። ባለስልጣናቱ ጥቅሉን ከፍተው ሰነዶቹን ከመረመሩ በኃላ ከፊሎቹን አስቀርተው የተረፈውን መልሰው ይሰጡዎታል። ወደተዘጋጀልዎት ማረፊያ እንደደረሱም፣ የማቋቋሚያ ድርጅቱ ሰራተኞች ሰነዶቹን ተቀብለው ኮፒ ካደረጉ በኃላ ይመልሱልዎታል።


DISTRICT OF COLUMBIA
REFUGEE
SERVICE CENTER
(A PROJECT OF ASSOCIATED
CATHOLIC CHARITIES)
1501 COLUMBIA ROAD, N.W.
HOURS: 9:00 AM - 5:00 PM
MONDAY THRU FRIDAY


OIM
IOM




IOWA
Refugee
Service Center
Iowa...A Place To Grow



የዩናይትድ ስቴትስን የማቋቋሚያ ፕሮግራም ልዩ የሚያደርገው በመንግስትና በግል ድርጅቶች ትብብር የሚካሄድ መሆኑ ነው። መንግስት ህግ ይቀርፃል፣ መመሪያዎች ያወጣል፣ ተቋቋሚዎች ለሚያገኟቸው አንዳንድ አገልግሎቶች ወጪ ይሸፍናል። ማቋቋሚያ ድርጅቶች ደግሞ የሚፈለገውን አገልግሎት ይሰጣሉ ተጨማሪ እገዛም ሊያበረክቱ ይችላሉ።

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመግባት ፍቃድ ያገኘ ማንም ስደተኛ፣ ከመምጣቱ በፊት እገዛ የሚያደርግለት ማቋቋሚያ ድርጅት ይመደብለታል። የማቋቋሚያ ድርጅቱ ሀይማኖታዊ፣ የግል፣ የስቴት ወይንም ብሄርን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል። ጉዳይዎን የያዘው የማቋቋሚያ ድርጅት፣ እርስዎ በሚሰፍሩበት አካባቢ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ወይንም ወኪል ይኖረዋል። በሚመደቡበት አካባቢ ዘመዶችዎ ካሉ፣ እርስዎን በማቋቋም ሊረዱ ይችላሉ። አንዳንድ ድርጅቶች እገዛ የሚሰጡ የበጎ ፈቃደኛ ሰራተኞች አሏቸው።

ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የማቋቋሚያ ድርጅቶች ከሀይማኖት ጋር የተያያዙ ቢሆኑም፣ እርስዎ ግን ሀይማኖታቸውን የመከተል ግዴታ የለብዎትም። ከዚህ በተጨማሪም የማቋቋሚያ ድርጅቶች፣ ስደተኞች የራሳቸውን የሀይማኖት ቡድን እንዲቀላቀሉ ማበረታታት አይፈቀድላቸውም።

እጉዞ መጨረሻ ሲደርሱም ዘመድዎ፣ ጓደኛዎ ወይንም ደግሞ የማቋቋሚያ ድርጅትዎ ወኪል አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ተገኝተው ይቀበልዎታል። ማረፊያ ቤት ይዘጋጅልዎታል። ይህም ለጊዜው የዘመድዎ ቤት፣ ሆቴል ወይንም እንደ አፓርትመንት ያለ ዘላቂ መኖሪያ ሊሆን ይችላል። (ስለ "መኖሪያ ቤት" በገፅ 27 ላይ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።)




የማቋቋሚያ ድርጅቱ ሰራተኞች፣ ዘመዶችዎ፣ ጓደኞችዎና የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች አዲስ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ እንዲለማመዱ እገዛ ይሰጣሉ። በእነርሱ እገዛም፤


- ዘላቂ መኖሪያ ያገኛሉ
- የቤት እቃና ልብሶች ያገኛሉ
- የማህበራዊ ዋስትና መታወቂያ ካርድ ማለት ሶሻል ሴኪዩሪቲ ካርድ ያገኛሉ (ለዚህ መታወቂያ ማመልከትዎን ማረጋገጥ ከቻሉ ጊዜ አንስቶ ስራ መፈለግ ይቻላሉ።)
- በአካባቢዎ ያለውን የህዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ይማራሉ
- ስለ አሜሪካ ህጎችና ደንቦች ማወቅ ይጀምራሉ
- ልጆችዎን ትምህርት ቤት ያስገባሉ
- ስራ ይይዛሉ
- ስለ ዩናይትድ ስቴትስ የገንዘብ አጠቃቀም ይማራሉ
- ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሳይዘገይ የጤና ምርመራ ወይንም ደግሞ ቀጣይ የህክምና ክትትል ያገኛሉ
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቶች ወይንም ደግሞ በጎ ፈቃደኛ አስተማሪዎች (ቱተሮች) ያገኛሉ
- በአካባቢዎ ስላሉ የኮሚዩኒቲ አገልግሎቶች ይረዳሉ

የማቋቋሚያ ድርጅቶች፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡ በኃላ ለመጀመሪያዎቹ ሰላሳ ቀናት የሚያስፈልጎትን መሰረታዊ ወጪ መሸፈን አለባቸው። አንዳንዶቹ ድርጅቶች ወጪውን ራሳቸው ይከፍላሉ። ሌሎች ደግሞ ገንዘቡን ለራስዎ ወይንም ለዘመድዎ ይሰጡና፣ ወጪዎን በከፊል ሆነ በሙሉ ራስዎ እንዲሸፍኑ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪ የማቋቋሚያው ድርጅት፣ ቢያንስ ለዘጠና ቀናት ምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ይሰጣል። ከዚያ በኋላ የሚሰጠው አገልግሎት እንደ ግለሰቡ ፍላጎትና እንደ ማቋቋሚያው ድርጅት ይለያያል። ለሚኖርዎት ጥያቄዎ ሆነ ለሚሹት አገልግሎት ወደ ሌሎች ድርጅቶች ሊመሩ ይችላሉ።

የማቋቋሚያ ድርጅቱ ወጪዎንም ሆነ እዳዎን የመክፈል ሀላፊነት የለበትም። ለወጪዎ ሀላፊው ራስዎ በመሆንዎ ስራ መስራት አለብዎት። ሰፈር ወይንም ከተማ ለመለወጥ ከፈለጉ ወጪዎን ራስዎ መቻል እንዳለበት ይገንዘቡ። ሰፈር ቀይረው በሚሄዱበት አካባቢ ያለ የማቋቋሚያ ድርጅት፣ እርስዎን የመርዳት ሀላፊነት የለበትም። መኖሪያዎን ለመለወጥ ሲወስኑ የራስዎ ሀላፊነት እንደሚሆን አይዘንጉ። መኖሪያዎን ስለ መቀየር ጥያቄ ካለዎት፣ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ሰራተኛ ያነጋግሩ።

አሜሪካውያን ራስን ለመቻል መርሆ ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ። ስለዚህም ኑሮዎን ለመገንባት በራስዎ አነሳሽነት ጥረት ማድረግ ይጠበቅብዎታል። ራስዎን በማቋቋሙ ረገድ ስኬትዎ የሚወሰነው፣ በሚያገኙት እገዛ ብቻ ሳይሆን በአመለካከትዎና በጥረቶችዎም ጭምር ይሆናል።


DRUG CENTERS



ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ በተጨማሪ፣ ሰዎች ራሳቸውን እንዲረዱ የሚያስችሉ የፌደራል ፕሮግራሞችና የኮሚዩኒቲ አገልግሎት ድርጅቶች አሉ። ስደተኞች የገቢ ድጎማና የቤተሰብ ምክር አገልግሎት የመሳሰሉ ማህበራዊ እገዛዎች ማግኘት ይችላሉ። ይሁንና አንዳንድ ልዩ አገልግሎቶች ከቦታ ቦታ እንደሚገኙበት ሁኔታ ይለያያሉ። በስደተኛነትዎ ተጨማሪ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ መሆንዎንና እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ማወቅ አለብዎት። የማቋቋሚያ ድርጅትዎ በአካባቢዎ ምን አይነት ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዳሉ ለማወቅ ይረዳዎታል።


ስራ እየሰሩ ራስዎን ለመቻል ጥረት ላይ ባሉበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጊዜያዊ እርዳታ የሚሰጡ ድርጅቶችና ፕሮግራሞች አሉ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት መመዘኛዎቹ የእርዳታው አስፈላጊነት፣ የገቢ መጠን፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ዕድሜና ሌሎች ነጥቦች ይሆናሉ። የሚገኙበት ሁኔታ ከተቀየረ ወይንም ደግሞ መመዘኛዎቹን ካላሟሉ የሚያገኙት እርዳታ ሊሰረዝ አሊያም ሊቀነስ ይችላል።

የማቋቋሚያው ድርጅት፣ እርስዎን ኢንፎርሜሽን በመስጠትም ሆነ ከኮሚዩኒቲ አገልግሎቶች ጋር በማገናኘት የመጀመሪያው ድልድይ ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጅቶች ወይንም አገልግሎቶች፣ በማቋቋሚያ ድርጅቶች አማካኝነት ያገኟቸዋል።

**የጋራ ተራድኦ ማህበራት** (MAAs)በበርካታ ኮሚኒቲዎች ይገኛሉ። በቀድሞ ስደተኞችና መጤዎች ማለት ኢሚግራንቶች ተመስርተው የራሳቸውን ሰው የሚረዱ ድርጅቶች ናቸው። አንዳንዶቹ የጋራ ተራድኦ ማህበራት ለስደተኞችና ለሌሎች መጤዎች ስለ ኮሚዮኒቲ ገለፃ ከመስጠት አንስቶ የትራንስፖርት ማለት የመጓጓዣ፣ የልብስና የቤት እቃ እገዛ ይሰጣሉ።







**የማህበራዊ አገልግሎት ድርጅቶች** ስደተኞችን ጨምሮ ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ድርጅቶች ልዩ ችግር ያለባቸውን ለምሳሌ ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆነ ቤተሰቦችን፣ ቤት የሌላቸውንና የአካል ጉዳተኞችን ይረዳሉ።

**የሀይማኖት ተቋማት** አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶችና ሙክራቦች ሲሆኑ ፀሎት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። አንዳንዶቹ ቤተ መፃህፍትያላቸው ሲሆን፣ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ ለልጆች ትምህርት ይሰጣሉ። ሌሎቹ ደግሞ የተለበሱ ልብሶችና የቤት እቃዎች ሲሰጡ፣ ለአዲስ መጤዎችና ለአረጋአውያን ፕሮግራሞች አሏቸው።

**ፉድ ስታምፕ** ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆነ ሰዎች ለምግብ መግዣ የሚሰጥ የፌደራል ፕሮግራም እርዳታ ነው። ስደተኞች፣ ፉድ ስታምፑን ወይንም የምግብ መግዣውን ኩፖን ለማግኘት አቅራቢያቸው ወዳለ የመንግስት ቢሮ ሄደው ማመልከት ይችላሉ። አመልካቾች ዝቅተኛ ገቢ እንዳላቸው ማረጋገጫና ስለ ግል ታሪካቸው ቅፅ መሙላት ይጠበቅባቸዋል። እርዳታው እንደ አመልካቹ የገቢ መጠንና የቤተሰብ ብዛት ይወሰናል። ፉድ ስታምፕ ለምግብ መሸመቻ ብቻ መዋል አለበት። ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮች ማለት እንደ ሲጋራ፣ የአልኮል መጠጥ፣ ዲያፐር (አላቂ የልጆች የሽንት ጨርቅ)፣ የወረቀት ውጤቶችና ሳሙና የመሳሰሉትን በፉድ ስታምፕ መግዛት አይቻልም።

**የኤሌክትሪክ ሀይልና ጋዝ እገዛ** ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች፣ ለክረምት ወራት ማሞቂያና የኤሌክትሪክ ወጪያቸውን ለመሸፈን የተነደፈ የፌደራል ፕሮግራም ነው። ስደተኞች አቅራቢያቸው ወዳሉ የመንግስት ቢሮዎች ሄደው እርዳታውን ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። አመልካቾች ስለገቢያቸውና ስለ ግል ታሪካቸው ቅፅ በመሙላት እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

**የገንዘብ እገዛ** ስራ ማግኘት ላልቻሉ ሰዎች መርጃ የታቀደ ፕሮግራም ሲሆን፣ በአካባቢ አስተዳደር ደረጃ የሚሰጥና ከኮሚኒቲ ኮሚኒቲ የሚለያይ ነው። ስደተኞች ወደ አካባቢያቸው አስተዳደር ሄደው ሊያመለክቱ ይችላሉ። አመልካቾች የገቢ ማረጋገጫና ስለ ግል ታሪካቸው ቅፅ መሙላት ይፈለግባቸዋል። የገንዘብ እርዳታው ለተወሰነ ወራት የሚሰጥ ሲሆን፣ አንዳንዴ ተጨማሪ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው። እነዚህም የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሚሆነው ግለሰብ ተግቶ ስራ መፈለጉ ወይንም ደግሞ በየጊዜው የስልጠና ፕሮግራሞች መከታተሉ ናቸው።



**ተጨማሪ የገቢ ዋስትና** Supplemental Security Income (SSI) የሚባለው ሲሆን እድሜያቸው 65 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ አረጋውያን፣ ለአይነ ስውራንና አካላቸው ለጎደለ ሰዎች የተቀረፀ ፕሮግራም ነው። እነዚህን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ስደተኞች አቅራቢያቸው ወዳለ የሶሻል ሴኪዩሪቲ ቢሮ ሄደው ማመልከት ይችላሉ። ይህ ቢሮ የሶሻል ሴኪዩሪቲ ካርድ የሚወጣበት ነው።

**ፖሊስ** የፖሊስ ሀላፊነት ህግ ማስፈፀምና የኮሚዩኒቲውን ደህንነት መጠበቅ ነው። በተጨማሪም ፖሊሶች፣ ከመደበኛ ስራቸው ውጪ ድንገተኛ የጤና ችግሮች ሲከሰቱ በመድረስና በማህበረሰቦች መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር አጋዥ ሚና ይጫወታሉ። መንገድ ለጠፋባቸው ሰዎችም ትክክለኛውን አቅጣጫ ያመላክታሉ።

ሁሉም ኮሚዩኒቲዎች **የእሳት አደጋ መከላከያና ድንገተኛ የህክምና አገልግሎት** አሏቸው። ድንገተኛ አደጋ ካጋጠሞትና አስቸኳይ እርዳታ ካስፈለግዎት፣በአብዛኛው የዩናይትድ ስቴትስ ግዛት ለእርዳታ ድረሱልኝ ተብሎ የሚደወልበት ቁጥር 911ነው። 911መደወል ካለብዎ ስልኩን ለሚቀበለው ሰው ስለ አደጋው ለመናገር ይዘጋጁ።

"ፖሊስ" ፣ "የእሳት አደጋ መከላከያ" ወይንም "አንቡላንስ" ያስፈልግ እንደሆነ ይግለፁ አድራሻዎንም ይንገሩ። የደረሰብዎትን ችግር በእንግሊዘኛ ለመግለፅ ከተቸገሩ ሄልፕ "Help" ወይንም ኢመርጀንሲ "Emergency" ካሉ በኋላ ስልኩን በቶሎ አይዝጉት። ስልኩ ክፍት ሲሆን ከየት እንደተደወለ ማወቅ ይቻላል።

በአካባቢዎ ያሉትን አገልግሎቶች ማወቅና አጠቃቀማቸውንም በሚገባ መረዳት፣ የዩናይትድ ስቴትስ ኑሮዎ እንዲቀል ያግዛል። እድለኛ ሆነው በአቅራቢያዎ ዘመድ ወይንም ቤተሰብ ካለዎ የእነሱ እገዛ በጣሙን ይጠቅማል። (ስለ ኮሚዩኒቲ አገልግሎቶች ተጨማሪ ዝርዝር ለማግኘት በገፅ 21፣ ስለ ትምህርት በገፅ 53 ስለ ጤና ደግሞ በገፅ 63 ላይ የተፃፉትን ይመልከቱ።)













መጀመሪያ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሲመጡ፣ የሚያርፉበት ስፍራ ተዘጋጅቶ ይጠብቅዎታል። የመጀመሪያ ቤትዎ መሰረታዊ የቤት መገልገያዎች ያሉት፣ ሰፈሩም ሰራተኞች የሚበዙበትና የተለያዩ ዘሮች ተደባልቀው የሚኖሩበት እንደሚሆን ይጠብቁ። የመጀመሪያ ማረፊያዎ ጊዜያዊ ሊሆን ይችላል። ቀደም ብለው ከተቋቋሙ ቤተሰቦች ጋር ወይንም ደግሞ በአፓርታማ፣ በሆቴል አሊያም ደግሞ በማቆያ ማዕከል (አብዛኛውን ጊዜ ከማቋቋሚያ ድርጅቶች ጋር የተያያዘ ነው) እንዲገቡ ሊደረግ ይችላል። ያላገቡ ወይንም ላጤ ከሆኑ ደግሞ፣ ቢያንስ በጊዜያዊነት ከሌሎች እርስዎን ከመሰሉ ስደተኞች ጋር ተዳብለው እንዲኖሩ ይደረጋል።

የማቋቋሚያ ድርጅቱ እርስዎ ዩናይትድ ስቴትስ ከደረሱ በኋላ ለአንድ ወር ያህል፣ ማረፊያ እንዲያገኙ የማድረግ ሀላፊነት አለበት። ከእርስዎ በፊት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጡ ዘመዶች ወይንም ወዳጆች ካለዎት፣ መኖሪያዎን እንዲያዘጋጁ ሊጠየቁ ይችላሉ። ለዚህም ከማቋቋሚያ ድርጅቱ የገንዘብ እገዛ ሊሰጣቸው ይችላል።

ዘላቂ መኖሪያዎን በተመለከተ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከደረሱ በኃላ ምክክር ይደረግበታል። ለበርካታ አሜሪካውያን፣ ተስማሚ የመኖሪያ ስፍራ ማግኘት ቀላል አይደለም። ለእርስዎም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይሆንም። የመጀመሪያ መኖሪያ ቤትዎ ኪራይ በእርግጥ በዋጋ የሚያዋጣዎ ቢሆንም የመጀመሪያ ምርጫዎ ላይሆን ይችላል። ጥሩ ሰፈርና የቤት አይነት፣ ለትምህርት ቤት፣ ለስራ፣ ለህዝብ ትራንስፖርትና ለገበያ ቅርብ እንዲሆን ይፈልጉ ይሆናል። መኖሪያ ቤት ሲፈልጉ፣ ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ ወኪል፣ ከቤተሰብዎና ከወዳጅ ዘመዶችዎ ጋር ይምከሩና የትኛው አካባቢ እንደሚሻል ሀሳብ ይቀበሉ። ቤት ፍለጋ ሳምንታት እንደሚፈጅ ይገምቱ።



በአብዛኞቹ የአሜሪካ ኮሚዩኒቲዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የመኖሪያ ቤት አይነቶች ይገኛሉ፤

- የአፓርታማ ህንፃዎች
- አንድ ቤተሰብ ብቻ የሚኖርባቸው ቤቶች
- ተንቀሳቃሽ ቤቶች
- በአፓርታማም ሆነ በግል ቤት ውስጥ የሚከራይ ክፍል

የመኖሪያ ቤቶች ሊያገኙ የሚችሉባቸው መንገዶች ፤

- ጓደኞች
- የስራ ባልደረቦች
- የማቋቋሚያ ድርጅት
- በህንፃ አጠገብ የተለጠፉ "ሬንት" ማለት የሚከራይ የሚሉ ምልክቶች
- በአፓርታማ ህንፃዎች ያሉ የአከራይ ቢሮዎች(ሬንታል ኦፊስ)
- የጋዜጣ ማስታወቂያዎች
- የቤት ሽያጭና ኪራይ ደላሎች ወይንም ተከራይና አከራይ አገናኞች (እነዚህ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ)



የአፓርታማ ኪራይ ቤቶች በአብዛኛው ምድጃ፣ ማቀዝገዣ (ፍሪጅ) የዕቃ ማጠቢያና ማድቤት፣ መታጠቢያ ቤት፣ አንድና ከዚያ በላይ መኝታ ቤቶች፣ ቁም ሳጥኖች፣ ሳሎንና ምግብ ቤት አላቸው። አነስ ባሉ አንዳንድ የአፓርታማ ኪራይ ቤቶች፣ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በአንድ ክፍል ውስጥ ተጠቃለው ይገኛሉ።

የቤት ኪራይ ከወር ወጪዎ አብዛኛውን እንደሚወስድ ይወቁ። የቤት ኪራይ ከስቴት ስቴት፣ ከከተማ ከተማ እንዲሁም ከሰፈር ሰፈር ይለያያል። የቤቱ ኪራይ የውሀ፣ የኤሌክትሪክ፣ የማሞቂያ፣ የጋዝ፣ ቆሻሻ ማስወገጃ የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ክፍያ ሊጠቀልል ይችላል። አሊያም ደግሞ እነዚህ አገልግሎቶች ለብቻ የሚከፈሉ ይሆናሉ። ቤት ለመከራየት ውል ከመፈረምዎ በፊት የእነዚህ አገልግሎቶች ዋጋ፣ በኪራዩ ይጠቃለል እንደሆነ ማወቁ ይጠቅማል።

አፓርታማ ወይንም ቤት ለመከራየት የኪራይ ውል (ሊዝ) መፈረም ይኖርብዎታል። ውሉ የተከራዩንና የአከራዩን መብቶች የሚያስጠብቅ ህጋዊ ሰነድ ሲሆን አከራዩ ወይንም የቤቱ ባለቤት አድልዎ እንዳይፈፅምብዎ ይከላከላል። አከራዮችም ሆኑ የቤት ባለቤቶች፣ የሚያከራዩት ቤት ቢያንስ ንፅህናውና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን፣ የመኖሪያ ቤት ህግ ይጠይቃል።



"ለእኛ በጣም ውብና ከዚህ ቀደም አይተን በማናውቃቸው ነገሮች የተሞላ አፓርታማ ነበር።



…ዛሬ ግን በዚህ ሰፈር የሚኖሩ ሰዎች በጣም ድሆች መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁ። አፓርታማዎቹም ትንንሽ ሳጥን መስለው ነው የሚታዩኝ።



ይሁንና ከልጆቹ ጋር ሆነን፣ ግድግዳው ጨረር ሲያገኘው እስከሚያበራ ድረስ ፈቅፍቀንና አሳምረን ደስ የሚል ቤት አደረግነው።"

የኪራይ ውል ማለት ሊዝ ሲፈርሙ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ተስማምተዋል ማለት ነው፤

- በአፓርተማው የሚኖሩ ሰዎች ብዛት
- የቤቱ ኪራይ መክፈል ያለበት ቀን (አብዛኛውን ጊዜ ወር በገባ እስከ አምስተኛው ቀን ድረስ ይሆናል)
- አፓርትመንቱ ጉዳት ሳይደርስበት በንፅህና መያዝ
- ቤቱን ለመከራየት የተስማሙበት ጊዜ (በአብዛኛው ለ12 ወራት ነው የሚሆነው)
- የኪራይ ስምምነቱ ማለት ሊዙ የሚሰረዝበት ሁኔታ

ሊዝ ከመፈረም በተጨማሪ፣ የቤት ኪራይ መክፈል የሚችሉ መሆንዎን ማረጋገጥ አለብዎት። ስራ ከሌለዎት ተያዥ ሆኖ የሚፈርምልዎ ሰው ያስፈልጋል "ኮ ሳይነር" "co-signer" የሚባለው ነው። አብዛኛውን ጊዜ ተከራዮች ውል ሲፈርሙ ቀብድ (ሴኪዩሪቲ ዲፖዚት) እንዲያስይዙ ይጠየቃሉ። ያስያዙት ገንዘብ ውሉ ሲያበቃና ቤቱን ለቀው ሲወጡ ይመለሳል።

በውሉ የሰፈሩትን ነጥቦች ካፈረሱ ከቤቱ ሊባረሩ ይችላሉ፣ ያስያዙት ገንዘብም ማለት ሴኪዩሪቲ ዲፖዚት አይመለስልዎትም።








14 Street - Union Sq
Station


ON RED
QUIET
ZONE
YIELD
STOP



በመላ ዩናይትድ ስቴትስ የህዝብ መጓጓዣ ማለት ትራንስፖርት በጣም የተለያየ ነው። በርካታ ከተሞች ከመሬት ስርና በላይ የሚጓዙ ባቡሮችና አውቶቢሶች የመሳሰሉ ሰፊ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህም ሰዎች ካለ ግል መኪና እንዲንቀሳቀሱ ያስችላል። ታክሲዎችም ቢኖሩም፣ አብዛኛውን ጊዜ ዋጋቸው ውድ ነው። በአንዳንድ ከተሞች ደግሞ የህዝብ ትራንስፖርት በቀላሉ አይገኝም። አሜሪካ እንደደረሱ በአካባቢዎ ስላለው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዝርዝር መረጃ ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ ያገኛሉ።

የህዝብ ትራንስፖርት በሌለበትና እንደልብ በማይገኝበት አካባቢ የሚኖሩ አዲስ መጤዎች፣ ቶሎ ብለው መኪና መግዛት ይኖርባቸዋል። ይሁንና በዩናይትድ ስቴትስ የመኪና ባለቤት ከመሆን ጋር የሚመጡ በርካታ ሀላፊነቶች አሉ።

በህጋዊ መንገድ መኪና ለመንዳት፣ የሚኖሩበት አካባቢ መንጃ ፈቃድ ያስፈልጋል። በዚህ ምትክ አለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድ መጠቀም አይቻልም። የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት የተወሰነው የዕድሜ ገደብ ከቦታ ቦታ ይለያያል። የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት በአቅራቢያዎ ወዳለ የተሽከርካሪዎች መምሪያ ሄደው የፅሁፍ፣ የእይታ ችሎታና የአነዳድ ፈተናዎች ማለፍ አለብዎት። አብዛኞች ስቴቶች መኪናዎች ኢንሹራንስ እንዲኖራቸው ያዛሉ።

> "አንድ ቀን በአውቶቡስ እየተጓዝኩ ሳለሁ ዙሪያዬን ስመለከት የተለያዩ ሰዎች አየሁ። ነጮች፣ አፍሪካ አሜሪካውያንና ሂዝፓኒኮች ነበሩ። አንዱ ሌላውን አያይም፣ ግድ ያለውም አይመስልም። ሰርቆ የሚያይ ወይንም እጅ የሚጠነቁል ሰው የለም። እኔም አውቶቢሱ ውስጥ ነበርኩ። ነገር ግን ምን እንደምመስል ማንም ደንታ ያለው መስሎ አልታየኝም።"




መኪና ለመግዛት ሲወስኑ ከዚህ በታች የየተዘረዘሩትን ወጪዎች ማጤን ያስፈልጋል።

- ኢንሹራንስ (ዋጋው ከስቴት ስቴት ይለያያል፣ በዩናይትድ ስቴትስ ነድተው ለማያቁ ሰዎች ደግሞ ይጨምራል።
- የመኪና ማስጠገኛ
- ነዳጅ
- ለመንጃ ፈቃድ፣ ለባለቤትነት ምዝገባ፣ ለመኪና ምርመራ ቦሎ የሚባለውና ቀረጥ
- የመኪና ማቆሚያ ቦታ ኪራይ

የመንጃ ፈቃድ ቋሚ መታወቂያ አይደለም። በየጊዜው መታደስ አለበት። አንዳንድ ህጎችን መጣስ የመንጃ ፈቃድ ሊያስነጥቅ ይችላል። ለምሳሌ አልኮል ጠጥቶ መንዳት መንጃ ፈቃድ ሊያስነጠቅ፣ የገንዘብ መቀጮ ሊያስከፍል አሊያም ደግሞ ሊያሳስር ይችላል።


## North America




New York → Los Angeles (2,911 Miles/4,684 Kilometers)
New York → Chicago (818 Miles/1,316 Kilometers)
New York → Miami (1,325 Miles/2,132 Kilometers


HELP WANTED
CALL FOR APPT 683-9035
TRUCK DRIVERS
CLASS-A VA. D.L. REQUIRED








Blue Bird School



በዩናይትድ ስቴትስ ስራ መስራት፣ ታላቅ ግምት ይሰጠዋል። ስለዚህም ለአዲስ መጪዎች ስራ ይዞ ራስን መቻል፣ ከሁሉም የሚቀድም ጉዳይ ሊሆን ይገባዋል። ስራው ጥሩ ክፍያ ባያስገኝም ወይንም ደግሞ ከዚህ ቀደም የሚሰሩት አይነት ባይሆንም እንኳን ቶሎ ስራ እንዲይዙ ይጠበቃሉ።

ዩናይትድ ስቴትስ እንደገቡ ከመጀመሪያ ግቦችዎ ቀዳሚው ስራ ፈልጎ መያዝ ይሆናል። ስደተኞችን ስራ በማስቀጠር ለመርዳት ከተቋቋሙ ድርጅቶች እገዛ ሊያገኙ ቢችሉም፣ የግል ጥረትዎና አመለካከትዎ በጣም ወሳኝ ነው። መንግስትም ሆነ የማቋቋሚያ ድርጅትዎ እርስዎን ስራ የማስቀጠር ሀላፊነት የለባቸውም። ለአንድ ስራ ከሌሎች አመልካቾች ጋር ሊወዳደሩ ስለሚችሉ አዎንታዊ አመለካከት መያዝና ለስራ ዝግጁነትዎን ማሳየት የእርስዎ ፋንታ ይሆናል።

የመጀመሪያ ስራዎ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ከሚይዟቸው በርካታ ስራዎች አንዱና በአሜሪካ ለሚገነቡት የስራ ልምድ ታሪክ ዋናው እርምጃ ይሆናል ለማለት ይቻላል። በትምህርትም ሆነ ከአሜሪካውያን ጋር በሚያደርጉት የዕለት ተዕለት ግንኙነት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታዎ እየተሻሻለ ሲመጣ፣ ወደ ተሻለና ክፍያውም ጥሩ ወደ ሆነ ስራ የመሸጋገር ዕድልዎም እንዲሁ እያደገ ይሄዳል። በመጀመሪያ ስራዎ ላይ ቢያንስ ለስድስት ወራት መቆየት ጥሩ የስራ ልምድ ታሪክ ለማካበት ይጠቅማል። በተቻለዎ መጠን ስራ ላይም ሆነ ሰፈር ውስጥ እንግሊዘኛ ለመናገር ቢሞክሩ ጠቃሚ ነው።



በዩናይትድ ስቴትስ ሴቶችም ወንዶችም ይሰራሉ። ሴቶች ከሰራተኛው ሀይል ግማሹን የያዙ ሲሆን በዮትኛውም ዘርፍ ወንዶች የሚሰሯቸውን ስራዎች ያከናውናሉ። እርስዎ በመጡበት ሀገር ሴቶች ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድ ይሆናል፣ ዳሩ ግን በዩናይትድ ስቴትስ የተለመደ ነገር ነው። ለቤተሰብዎ ከሁለት በኩል የሚገኝ ገቢ ማለት እርስዎም ባለቤትዎም ቢሰሩ፣ በገንዘብ ራስን የመቻል እድልዎ ሰፊ ይሆናል። እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆነ ልጆች፣ የትርፍ ሰዓት ስራ መስራት ይችላሉ። በርካታ ወጣቶች የመጀመሪያ ስራቸውን የሚጀምሩት፣ ከትምህርት ሰዓት ውጪና ትምህርት ቤት በማይዘጋበት የዕረፍት ጊዜ ነው።


የመጀመሪያ ግብዎ የተገኘውን ስራ መስራት ቢሆንም የተሻለ ስራ ለመያዝ የረጅም ጊዜ እቅድ መንደፍ አለብዎት። ይህም የተሻለ ስራ ለማግኘት ስልጠና መውሰድ፣ የስራ ሙያ ለውጥ ማድረግ ወይንም ቀድሞ ይሰሩበት ወደነበረው ሙያ መመለስ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ደግሞ በሚገባ ማቀድ፣ የስራ ገበያን ማጥናትና በአንድ ሙያ ለመስራት የሚያስፈልገውን ሰርተፊኬት ወይንም ፈቃድ ለማግኘት መመዘኛዎች ማሟላት ይጨምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ ትዕግስተኛ መሆን ያስፈልጋል። ስለዚህ ጉዳይ በአካባቢዎ ካለ የቅጥር አማካሪ፣ ከሚቋቋሚያ ድርጅትዎ ወይንም በአቅራቢያዎ ካለ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ።

ከሁሉም በላይ ልብ ሊሉት የሚገባው ነገር ቢኖር፣ ዩናይትድ ስቴትስ ጠንክሮ ለሰራባት የዕድሎች ምድር መሆኗን ነው። በርካታ አሜሪካውያን በመንግስት የገንዘብ ድጎማ ከመተማመን ይልቅ፣ ራስንና ቤተሰብን ለማስተዳደር መስራት አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ጥሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ መኖር ለተሻለ የስራ እድል የሚያበቃ በመሆኑ፣ በርካታ ስደተኞች ስራ እየሰሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል ይጥራሉ። መጀመሪያ ላይ የአሜሪካ ኑሮ ግራ የሚያጋባ ቢመስልም፣ ጊዜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ስለ አዲስዋ አገርዎም ሆነ ስለምትሰጠው እድል የበለጠ እያወቁ ይሄዳሉ።

## ስራ ፍለጋ

ስራ ፍለጋ ላይ አመለካከትዎ ወሳኝ ነው። ቀጣሪዎች እርስዎን የሚገመግሙት በአኳኋንዎና በአቀራረብዎ ነው። እንግሊዘኛ ባይናገሩም ወይንም ደግሞ እውቀትዎ ውሱን ቢሆንም፣ ፈገግታ የተላበሰ ፊትና የስራ ጉጉት ማሳየት በጣም ይጠቅማል። ለስራ ቃለ መጠይቅ ሲጠሩ በሰዓቱ ይድረሱ። ደህና ለብሰውና ንፁህ ሆነው ይቅረቡ። በቃለ መጠይቁ ወቅት ሊፈሩና ሊጨነቁ ስለሚችሉ ይረጋጉ። በዩናይትድ ስቴትስ የኖረ ልምድ ያለው ሰው እንኳን በእንዲህ አይነት ሁኔታ መጨነቁና መጠበቡ አይቀርም። ከመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ በኋላ ስራው ባይሳካልዎት ተስፋ አይቁረጡ። አንድ ስራ ለማግኘት በርካታ ቃለ መጠይቆች ማድረግ ሊኖርብዎ ይችላል። በዩናይትድ ስቴትስ ላሉ ስራ ፈላጊዎች ይህ የተለመደ ነገር ነው።

የመጀመሪያ ስራዎን ለማግኘት ከማቋቋሚያ ድርጅቱ ወይንም ከስደተኛ ስራ አስቀጣሪ አገልግሎት እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ። የማቋቋሚያ ድርጅትዎ ሰራተኞች፣ ስለ ስደተኞች ስራ አቀጣጠር ልምድ አላቸው። ሌሎች በርካታ ስደተኞች በዩናይትድ ስቴትስ የመጀመሪያ ስራቸውን እንዲይዙ ረድተዋል። ሀሳብዎን ያካፍሏቸው ምክራቸውንም ይቀበሉ። በዕውቀትዎና በችሎታዎ ምን አይነት ስራ ሊያገኙ እንደሚችሉ በግልፅ ይነግርዎታል።





"በርካታ የዩናይትድ ስቴትስ ጋዜጦች፣ ክፍት ስራ ቦታዎች የተዘረዘሩባቸው "Help Wanted" ወይንም "Employment" የተሰኙ አምዶች አሏቸው።"


ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ስቴት ያለ ክፍያ የሚሰሩ ስራ አስቀጣሪ ድርጅቶች አሉት። እነዚህ ድርጅቶች የት የት እንደሚገኙ የማቋቋሚያ ድርጅቱ ይነግሮታል።

ጓደኞች፣ ዘመዶች እንዲሁም ከእርስዎ ቀድመው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጡ የስደተኛ ኮሚዩኒቲ አባላት ስለ ክፍት የስራ ቦታዎች ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በርካታ የዩናይትድ ስቴትስ ጋዜጦች ክፍት ስራ ቦታዎች የተዘረዘሩበት "Help Wanted" ወይንም "Employment" የተሰኙ አምዶች አሏቸው።"

ስራ አስቀጥረው ክፍያ የሚጠይቁ የግል ድርጅቶች አሉ። አንዳንዶቹ ድርጅቶች የሚጠይቁት ክፍያ በጣም ውድ ሊሆን ስለሚችል፣ ኮንትራት ከመፈራረምዎ አስቀድሞ ፖሊሲዎቻቸውን በሚገባ መረዳት አለብዎት። ያልገባዎት ነገር ካለ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን እርዳታ ይጠይቁ።




"ስራ ለመስራት የሚያስችል የስራ ፈቃድ እንዳልዎት ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። በርካታ ስደተኞች፣ በስራ ፈቃድ ሰነድ ማለትም በEmployment Authorization Document (EAD)፣ የዜግነትና የኢሚግሬሽን አገልግሎት CIS ማህተም ባደረገበት I-94፣ በሶሻል ሴኪዩሪቲ ካርድና ፎቶ ባለበት መታወቂያ (የመንጃ ፈቃድ ወይንም ፓስፖርት ሊሆን ይችላል) በመጠቀም ስራ መስራት ይችላሉ። ምን ጊዜም ቢሆን ለስራ ቃለ መጠይቅ በሚቀርቡበት ጊዜ ዋነኛውን ሰነድ ይዘው መቅረብ አለብዎት። ቅጂ ወይንም ፎቶ ኮፒ ተቀባይነት የለውም።"



## የህፃናት መዋያ (ዴይ ኬር)

በበርካታ የአሜሪካ ቤተሰቦች እናትም አባትም የሙሉ ቀን ሰራተኞች ይሆናሉ። ይህ ማለት ደግሞ ልጆቻቸው ሙሉ ቀን የሚውሉበትንና የሚጠበቁበትን ስፍራ ማመቻቸት አለባቸው ማለት ነው። ልጆቹ ከፍ ያሉ ከሆኑ ደግሞ፣ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊትና በኋላ የሚቆዩበት ስፍራ መመቻቸት አለበት። አንዳንድ ትምህርት ቤቶችና የግል ኩባንያዎች እንዲህ አይነቱን አገልግሎት ይሰጣሉ፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን ያስከፍላሉ። በመኖሪያ ቤታቸው ወይንም ሰፈር ውስጥ የህፃናት መዋያ አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች አሉ። ከማቋቋሚያ ድርጅት ሰራተኛ ስለ ዴይ ኬር አገልግሎት ምክር ሊያገኙ ይችላል።

## የስራ አይነቶች

በዩናይትድ ስቴትስ የተለያየ ልምድና ስልጠና የሚሹ ሶስት አይነት ስራዎች አሉ፤

## የመጀመሪያ ደረጃ ስራዎች

እነዚህ ስራዎች አነስተኛ ልምድና ስልጠና የሚጠይቁ ሲሆን፣ የሆቴል ክፍል ፅዳት፣ ረዳት የምግብ ቤት አስተናጋጅ ወይንም የፋብሪካ ሰራተኛ የመሳሰሉት ናቸው። ክፍያቸውም በሰዓት ሲሆን ከፍተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ አይጠይቁም። በርካታ ስደተኞች እንደዚህ አይነቶቹን ስራ እየሰሩ እንግሊዝኛ ይማራሉ ሌሎች ስልጠናዎችን ይወስዳሉ።

## ችሎታ ጠያቂ ስራዎች

የእነዚህ ስራዎች ክፍያ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ስራዎች የተሻለ ነው። የተሻለ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀት፣ስልጠናና ችሎታን ማሳየት ይጠይቃሉ። የአውቶሞቢል መካኒክ፣ የውብት ሳሎን ሰራተኛ፣ ኤሌክትሪሺያን፣ የኮምፒውተር ጥገናን የመሳሰሉ ስራዎች ችሎታ ጠያቂ ናቸው። በአጠቃላይ የችሎታ ጠያቂ ስራዎች ክፍያ፣ በሰዓት ወይንም በሳምንት ሊሆን ይችላል። ደሞዙም ከአብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ ስራ እንዳውም ከአንዳንድ የሙያ ስራ ይበልጣል። በርካታ ችሎታ ጠያቂ ስራዎች ላይሰነስ ማለትም



ስራ መስራት የሚያስችል ፍቃድ ወይንም የሙያ ማህበር አባል መሆንን ይጠይቃሉ። በሀገርዎ የነበረዎት ፍቃድ በዩናይትድ ስቴትስ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል።

## የሙያ ስራዎች

በአብዛኛው ቢያንስ የኮሌጅ ዲግሪ፣ከፍተኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታና በተወሰነ ሙያ ስልጠናና ችሎታ ይጠይቃሉ። እነዚህን ስራዎች ለማግኘት ረዥም ጊዜ የሚወስድ ሲሆን፣ ምን አልባትም በአገርዎ የወሰዱትን የሙያ ስልጠና ደግመው መማሩ የግድ ሊሆን ይችላል። በርካታ የሙያ ስራዎች ማለት እንደ ህክምናና የጥርስ ህክምና አይነቶቹን ለማግኘት፣ የሚሰሩብትን ስቴት ላይሰንስ ማለት ፍቃድ ወይንም ሰርቴፊኬት ማግኘት ይስፈልጋል። ሀገርዎ እያሉ ፍቃድ ያለዎት ቢሆንም እንኳ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ለመስራት ተጨማሪ ጥናቶች ማካሄድና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት አለብዎት። የአብዛኞቹ የሙያ ስራዎች ክፍያ በሰዓት ሳይሆን በሳምንት ወይንም በወር የሚተመን ደሞዝ ነው።

ስራን በተመለከተ የአጭርና የረጅም ጊዜ የስራ ግብዎን በሚያቅዱበት ጊዜ መዘንጋት የሌለብዎት ነገር፣ ካሰቡት ደረጃ ለመድረስ በርካታ ስራዎች መስራት እንደሚኖርብዎ ነው። ምን አልባት ይህ ሁኔታ በሀገርዎ ከነበረዎ ተሞክሮ ጋር ሲነፃፀር የተለየ ሊሆን ይችላል። ይሁንና አብዛኞች አሜሪካውያን በስራ ህይወታቸው፣ ከሶስትና ከአራት ጊዜ በላይ ስራ ይቀይራሉ።

## ደሞዝ፣ ተቀናሽ ሂሳብና ጥቅማ ጥቅሞች

ስለ ደሞዝና ክፍያ፣ ሁሉንም የስራ አይነቶች የሚመለከቱ የፌደራልና የስቴት ህጎች አሉ። ስራ ከመቀጠርዎ በፊት ምን ጊዜም ስለ መደበኛው ክፍያ ማለት ስለ ደሞዙ ለማወቅ ይሞክሩ። ካልገባዎም ይጠይቁ። ከደሞዙ በተጨማሪ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህንም አጣርተው ይወቁ። አንዴ ከተቀጠሩ በኋላ ስለ አመታዊ የደሞዝ ክፍያዎ፣ ለአገር ውስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ማለት ለIRS የሚላክ ቅፅ እንዲሞሉ ይደረጋል።

ደሞዝዎ በየጊዜው በቼክ ይሰጥታል። ይህም በሳምንት፣ በአስራ አምስት ቀን ወይንም በወር ሊሆን ይችላል። አንዳንድ አነስተኛ ድርጅቶች ደሞዝ የሚከፍሉት በካሽ ማለት በጥሬ ብር ነው። ይሁንና ሁል ጊዜ ስለ ክፍያው ደረሰኝ ሊደርስዎ ይገባል። በደረሰኙ ላይ ስንት ሰዓት እንደሰሩ፣ የተጣራውና ያልተጣራው ክፍያና ተቀናሽ ሂሳቦች መዘርዘር አለባቸው። የመጀመሪያ ደሞዝዎ ደረሰኝ ግራ ሊያጋባዎ ስለሚችል፣ ያልገባዎት ነገር ካለ ጓደኛዎን ፣ ዘመድዎን ወይንም ደግሞ የማቋቋሚያ ድርጅቱን ሰራተኛ ይጠይቁ። ግልፅ ማብራሪያ ያገኛሉ። ምን ጊዜም ቢሆን በክፍያ ቼኩ ላይ የተጠቀሰው መጠንና ተቀናሽ ሂሳቦች በትክክል መሰላታቸውን ማመሳከር ይገባል።

**ያልተጣራ ክፍያ**፣ግሮስ ፔይ የሚባለው ሲሆን አንድም ተቀናሽ ሳይደረግበት የሚያገኙት ጠቅላላ ደሞዝ ነው። በቼኩ ላይ የተፃፈው ያልተጣራ ክፍያ መጠን፣ የሰሩት ሰዓት በክፍያ ተባዝቶ ከሚሰላው መጠን ጋር መስተካከል አለበት።

**ተቀናሽ ሂሳብ** ካልተጣራ ክፍያ የሚቀነሱ ሂሳቦች ናቸው። እነዚህም የፌደራል ቀረጥ፣ የማህበራዊ ዋስትና ሶሻል ሴኪዩሪቲ፣ ህክምና ነክ (ሜዲኬር) በአብዛኛው ግዛቶች ደግሞ የስቴት ታክስ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ እርስዎ በምርጫዎ የሚከፍሏቸና ለጤና ኢንሹራንስ፣ ለሰራተኛ ማህበራት፣ ለህይወት ኢንሹራንስና ለቁጠባ ማህበር ወጪ የሚሆኑት፣ በተቀናሽ ሂሳቦች ውስጥ ይካተታሉ።



**የተጣራ ክፍያ** ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቆረጡ በኃላ እጅዎ የሚገባው የተጣራ ክፍያ ነው።

**ጥቅማ ጥቅሞች** ከላይ በተገለፀው መልኩ ከእርስዎና ከሌሎች በተሰበሰበ ቀረጥ በኩል፣ በቀጥታ ከአሰሪዎ ኩባንያ አሊያም ከመንግስት የሚገኝ ነው።

**የጤና ኢንሹራንስ** ከጥቅማ ጥቅሞች አንዱ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል በአሰሪዎ፣ ቀሪው ደግሞ በእርስዎ የሚሸፈን ነው። አንዳንድ ኩባንያዎች ሰራተኞታቸው የጤና ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ከመሆናቸው በፊት፣ የተወሰነ ማለት ከሶስት እስከ ስድስት ወራት ላለ ጊዜ እንዲሰሩ ያደርጋሉ። በአብዛኞቹ የጤና ኢንሹራንሶች ጥቂት ክፍያ ጨምሮ ቤተሰብን ማካተት ይቻላል። አሰሪዎች በሙሉ ለሰራተኞቻቸው የጤና ኢንሹራንስ ባይሰጡም አብዛኞቹ ግን ይሰጣሉ። በዩናይትድ ስቴትስ የህክምና ወጪ በጣም ውድ በመሆኑ የጤና ኢንሹራንስን ጉዳይ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ ከአሰሪዎ ሊያገኙ የሚችሏቸው ጥቅማ ጥቅሞች **የህመም ፍቃድ፣ የእረፍት ፈቃድና ጡረታ** ናቸው።

የኩባንያ ማለት የድርጅት ፖሊሲዎች ስለሚለያዩ፣ ገና ሲቀጠሩ ስለሚሰሩበት ድርጅትም ሆነ ኩባንያ ብዙ ለማወቅ ይሞክሩ። በአንዳንድ ኩባንያዎች፣ የአገልግሎት ዘመን በጨመረ ቁጥር ጥቅማ ጥቅሞቹም እንዲሁ ይጨምራሉ። ለምሳሌ የብዙ አመት አገልግሎት ያላቸው ሰራተኞች፣ ከአዲስ ተቀጣሪዎች የበለጠ የአመት እረፍት ይሰጣቸዋል። መስሪያ ቤትዎ ስለሚሰጣቸው ጥቅማ ጥቅሞች በትክክል ለመረዳት የፐርሶኔልን ቢሮ፣ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ሰራተኞች፣ ጓደኞችዎን ወይንም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲመጡ ሀላፊ የሆነለዎትን ግለሰብ ማለት ስፖንሰሮን መጠየቁ ይጠቅማል።

ሌሎች ከስራ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጥቅማ ጥቅሞች ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው።

**ሶሻል ሴኪዩሪቲ** የፌደራል መንግስት የጡረታ ኢንሹራንስ ፕሮግራም ነው። ወጪው የሚሸፈነው በአሰሪው ኩባንያና በሰራተኞች ነው። የሶሻል ሴኪዩሪቲ ጥቅም በዩናይትድ ስቴትስ የደሞዝ ክፍያ ታሪክዎ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ተጠቃሚ የሚሆኑትም በታክስ አማካኝነት ለፕሮግራሙ አስተዋፅኦ ያደረጉ ግለሰቦች ናቸው።

**የስራ አጥ ኢንሹራንስ** አሰሪው በሚከፍለው ቀረጥ የሚደገፍ ሲሆን፣ ተጠቃሚዎቹም ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ስራ ያጡ ሰዎች ናቸው።






Kelly INN














Mobil Servi







**የሰራተኞች ካሳ ክፍያ** በአብዛኞቹ ስቴቶች ያለ ፕሮግራም ነው። ስራ ላይ ሆነው ጉዳት ለደረሰባቸው ሰራተኞች፣ ደሞዝ በመክፈልም ሆነ የህክምና ወጪያቸውን በመሸፈን ይሰጣል።

## የቅጥርና የስራ መብቶች

በስደተኛነትዎ እንደ ማንኛውም አሜሪካዊ ዜጋ በዩናይትድ ስቴትስ የመስራት መብት አለዎት። አንድ ቀጣሪ፣ ስደተኛ በመሆንዎ አድልዎ ሊፈፅምብዎ ወይንም ደግሞ በእድሜዎ፣ በቀለምዎ፣ አካልዎ በመጉደሉ፣ በማግባትዎ፣ በዘርዎ፣ በብሄርዎ፣ በዜግነትዎ፣ በሀይማኖትዎም ሆነ በፆታዎ ስራም ሆነ እድገት ሊነፍግዎት አይችልም። ይሁንና አንዳንድ ስራዎች ማለትም የመንግስት በሆኑት ለመቀጠር፣ የግድ የአሜሪካ ዜጋ መሆን ያስፈልጋል። ስራን አስመልክቶ የተደነገጉ ህጎች፣ ሰራተኞች ደህንነታቸው ሳይጠበቅና ፆታዊ የመዳፈር ብልግና ባለበት ሁኔታ እንዳይሰሩ ይከለክላል።

## ለስራ ስኬት ጠቃሚ ምክሮች

የማቋቋሚያ ድርጅቶችም ሆኑ በርካታ ስደተኞች፣ ዩናይትድ ስቴትስ ገብተው ገና የመጀመሪያ ስራዎን እንደያዙ፣ ልብ ሊሉ የሚገባዎ ነገሮች መኖራቸውን ይገልፃሉ። እነዚህ ነገሮች በስራዎ እንዲረጉ ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት ተራምደው የተሻለ ስራ እንዲይዙም ሆነ እድገት እንዲያገኙ ይጠቅማሉ።

የስራ ሰዓት ያክብሩ፣ አያርፍዱ። በዩናይትድ ስቴትስ ሰዓት ማክበር ታላቅ ግምት ይሰጠዋል። ስራዎ ላይ ሁል ጊዜ በሰዓት የሚገኙ ከሆነ፣ አለቃዎ ስለ እርስዎ አዎንታዊ ግምትና አመለካከት ይኖረዋል። ካረፈዱ፣ የዘገዩበት ጊዜ ተሰልቶ ከደሞዝዎ ይቆረጣል። የህመም ፈቃድ ሲታመሙ ብቻ ይውሰዱ። አሜሪካውያን በአብዛኛው ጉንፋንን ለመሳሰለ ቀላል ህመም ከስራ አይቀሩም። ይህን በማድረጋቸውም ይኮራሉ።

ምን ጊዜም ቢሆን በሆነ ምክኒያት ቢያረፍዱም ሆነ ቢቀሩ የቅርብ አለቃዎን ያስታውቁ። ከአለቃዎና ከስራ ባልደረቦችዎ ጋር ይግባቡ። ለዚህም የምሳ ሰዓትና የሻይ እረፍት ጥሩ አጋጣሚ ናቸው። የአየር ጠባይ ሁኔታ፣ የቅዳሜና እሁድ እረፍት፣ ምግብና ስፖርት በዩናይትድ ስቴትስ ጥሩ የመነጋገሪያና የመግባቢያ ርዕሶች ናቸው። እንደዚህ አይነቱ አጋጣሚ፣ በተለይ በበዓል ሰሞን ባህልዎንና ልምድዎን ለሌሎች ለማስተዋወቅ እድል ይፈጥራል።


በስራዎ ውጤታማ ይሁኑ፣ ከስራ ባልደረቦችዎና ጓደኞችዎ ጋር በወሬ ሳይጠመዱ ተግባቢ መሆን ይችላሉ። ስራ ላይ ያልገባዎት ነገር ካለ ይጠይቁ። በስራ ሰዓት በግል የስልክ ወሬ ከመጠመድ ይቆጠቡ።

ጥያቄ ይጠይቁ፣ አንድ ነገር ካልገባዎት የስራ ባልደረባዎንም ሆነ አለቃዎን ከመጠየቅ አይቦዝኑ። ያልገባዎን በመጠየቅ የተሻለ ስራ ማከናወን ይችላሉ፣ አለቃዎም ስለ እርስዎ ጥሩ ግምት ያድርበታል።

በራስዎ ተነሳሽነት አዳዲስ ስራዎች ለመማርና ተጨማሪ ሀላፊነቶች ለመውሰድ ይጣሩ። በማንኛውም የስራ መስክ ማደግ የሚቻለው፣ ተጨማሪ ሀላፊነቶችን ለመውሰድ በሚያሳዩት ፍላጎትና ፈቃደኝነት ነው።

በሌላ ኩባንያም ሆነ ድርጅት የተሻለ ስራ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ እድል ከገጠምዎት፣ ምንጊዜም ቢሆን ጥለው የሚሄዱትን መስሪያ ቤት አለቃ፣ ሁለት ሳምንታት ቀድመው ያስታውቁ። ስራ ማግኘትዎን ሳያረጋግጡ በምንም አይነት የያዙትን ስራ አይልቀቁ። ጥሩ የስራ ሬኮርድ ለማስመዝገብም፣ በመጀመሪያ ስራዎ ላይ ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ይቆዩ።





እድሜ፣ ዘር፣ ሀይማኖትና መደብ ሳይል በዩናይትድ ስቴትስ ሁሉም መማር ይችላል። የህዝብ ትምህርት ቤቶች ነፃ ሲሆኑ፣ እድሜያቸው 6-16 የሆነ ልጆች እንዲማሩ በህግ ተደንግጓል። እንደየአካባቢው የትምህርት ፖሊሲ፣ ከተወሰነ የእድሜ ክልል በላይና በታች ላሉ ልጆች ነፃ ትምህርት ሊሰጥ ይችላል። ወላጆች ልጆቻቸውን በግል ት/ቤቶች ማስተማር ይችላሉ። አብዛኞቹ የግል ት/ቤቶች የሀይማኖት ዝንባሌ አላቸው፣ ክፍያቸውም በጣም ውድ ነው። ከሁለተኛ ደረጃ በላይ የሚሰጥ ትምህርት ውድ ሊሆን ይችላል።

በርካታ አሜሪካውያን፣ ጥሩ ስራ ለማግኘትና የተሻለ ህይወት ለመምራት ትምህርት ወሳኝ ነው ብለው ያምናሉ። በትምህርት ለመግፋት የሚወስኑ አዋቂዎች በአብዛኛው ቀን ቀን ሙሉ ስራ እየሰሩ፣ ማታ ማታና ቅዳሜና እሁድ ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ።

## የልጆች የህዝብ ትምህርት ቤት (ፓብሊክ ስኩል)

በአሜሪካ የህዝብ ወይንም የመንግስት ት/ቤቶች፣ ከተለያየ ዘር፣ ሀይማኖትና መደብ የሆኑ ልጆች በመማሪያ ክፍሎችና ከትምህርት ውጪ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች አብረው የሚውሉባቸው ስፍራዎች ናቸው። የአካል ጉዳት የደረሰባቸውና የአዕምሮ ችግር ያለባቸው ልጆች፣ ት/ቤት ገብተው መማር አለባቸው። ትምህርት ቤቶቹ የልጆቹን ችግር ከገመገሙና ከወላጆቻቸው ጋር ከመከሩ በኃላ ስለትምህርታቸው እቅድ ያወጣሉ።

ልጆችዎ እዚህ ሀገር እንደገቡ ወዲያውኑ ት/ቤት መግባት አለባቸው። የማቋቋሚያ ድርጅቱ ልጆችዎ ት/ቤት እንዲገቡ ይረዳል። አብዛኞቹ ት/ቤቶች ፣ አዲስ ገቢ ተማሪዎች የክትባትና የጤና መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠይቃሉ። የህዝብ ት/ቤቶች ነፃ ይሁኑ እንጂ እርሳስ፣ ደብተር፣ ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎችና የአንዳንድ ልዩ እንቅስቃሴ ወጪዎች የሚሸፈኑት በወላጆች ይሆናል።




በአጠቃላይ ሶስት አይነት የትምህርት ደረጃዎች አሉ። **የአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣** ከመዋለ ህፃናት አንስቶ እስከ አምስተኛ ወይንም ስድስተኛ ክፍል ያለው ሲሆን በአምስት አመት ይጀመራል። **መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣** በአብዛኛው ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለው ነው። **ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ** ደግሞ የመጨረሻው ሲሆን፣ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያለውን ይሸፍናል። ከፍተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ዲፕሎማ ይሰጣቸዋል። የአዲስ ገቢ ተማሪዎች የክፍል ምደባ በአብዛኛው የሚከናወነው፣ በዕድሜያቸውና ቀደም ሲል በነበራቸው የትምህርት ደረጃ መሰረት ይሆናል። ብዙ እንግሊዘኛ የማይችሉና በእድሜ አነስ ያሉ ልጆች፣ ዝቅ ወዳለ ክፍል እንዲከለሱ ይደረጋል።

በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱት በነሀሴ ወይንም በመስከረም ሲሆን በግንቦት ወይንም በሰኔ ይዘጋሉ። የሚበዙት ተማሪዎች ከሰኞ እስከ አርብ በየቀኑ ለስድስት ሰዓት ይማራሉ። ቤትዎ ከትምህርት ቤቱ የራቀና ለልጆችዎ የእግር ጉዞ ሩቅ ከሆነባቸው፣ ትምህርት ቤቱ ነፃ የአውቶቢስ አገልግሎት ሊሰጣቸው ይችላል። ልጆች ምሳ ይዘው ሊሄዱ



ይችላሉ አሊዚያ ደግሞ ከትምህርት ቤቱ ካፊቴሪያ ማለት ምግብ ቤት በተመጣጣኝ ዋጋ ሰውኑት ገንቢ ምግብ ገዝተው መብላት ይችላሉ።

ከትምህርት ገበታ አለመቅረት እጅግ ጠቃሚ ነው። ተማሪዎች ትምህርት ቤት ካልመጡ፣ የቀሩበትን ምክኒያት የሚገልፅ ደብዳቤ ከወላጆች አፅፈው ማምጣት አለባቸው። ከክፍል የቀረ ተማሪ ያመለጠውን የትምህርት ሰዓት ማካካስ ይጠበቅበታል።

በሁሉም የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ነው የሚማሩት። የአሜሪካ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ከሌሎች ሀገሮች የተለየ ሊሆን ይችላል። መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲሸመድዱ ሳይሆን ሀሳብ እንዲያፈልቁ፣ እንዲመራመሩና እንዲያስቡ ይገፋፉቸዋል። ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውሱን ቢሆንም እንኳ፣ ጥያቄ እንዲጠይቁና በውይይቶች እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

በዩናይትድ ስቴትስ፣ አንድ ወጥ የሆነ ብሄራዊ ስርዓተ ትምህርት ማለት ካሪኩለም የለም። ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው የሚወሰነው፣ በእያንዳንዱ ስቴትና በአካባቢ የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ነው። ነገር ግን እንግሊዘኛ፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ ሳይንስ (ሶሻል ስተዲ)፣ ሳይንስና የአካል ማጎልመሻ ትምህርቶች በመደበኛነት ይሰጣሉ።

እንደ ተማሪዎች ምርጫ ደግሞ የስነጥበብ፣ የሙዚቃና የውጪ ቋንቋዎች ትምህርቶችም አሉ። በርካታ ትምህርት ቤቶች በተለይ የሁለተኛ ደረጃዎቹ ከመደበኛ ትምህርቶች ሌላ በትምህርት ሰዓትም ሆነ ከትምህርት ሰዓት ውጪ፣ ተማሪዎቻቸውን በተለያዩ የስፖርትና የክለብ እንቅስቃሴዎች ያሳትፋሉ።

ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች ትልቁ ፈተና፣ በተለይ የቤት ስራቸውን ሊያሰራ የሚያስችል እንግሊዘኛን መማርና ማወቅ ይሆናል። አብዛኞቹ ቶሎ ይለምዳሉ። በርካታ ትምህርት ቤቶች ለአዲስ ገቢዎች ልዩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣሉ። እንግሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ English as a Second Language ESL ይባላል። ሌሎች ትምህርት ቤቶች ደግሞ የቋንቋ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች፣ ልዩ መምህር ወይንም አስጠኚ ይመድባሉ። በርካታ አዲስ ገቢ ተማሪዎች በመጀመሪያው የትምህርት አመት የመልመድ ችግር ይገጥማቸዋል፣ ብቸኝነት ይሰማቸዋል። ዳሩ ግን የመግባባት ችሎታቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር፣ ጓደኛ እያፈሩና እየተለማመዱ ይሄዳሉ።

የአሜሪካውያን ተማሪዎች አለባበስ፣ በርካታ ተማሪዎችንና ወላጆችን ያስገርማል። የአሜሪካ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎቻቸው ነፃነት ቢሰጡም ቅሉ፣ ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ስርዓትና ደንብ ማክበር አለባቸው። የትምህርት ቤቱን ህግና ደንብ ሲጥሱ ተጨማሪ የቤት ስራ እንዲሰሩ፣ ከትምህርት ሰዓት ውጪ በትምህርት ቤት እንዲቆዩ ወይንም ደግሞ በአንዳንድ እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፉ ይደረጋል። ለጥቂት ቀናት ከትምህርት ቤት የሚታገዱበት ሁኔታም አለ። በአብዛኞቹ የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤቶች የአካል ቅጣት ፈፅሞ ክልክል ነው።

በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በተለይም በትልልቅ ከተማዎች በሚገኙት ውስጥ፣ የወጣት ወንበዴ ቡድኖች (ጋንጎች) እንዲሁም በዘርና በብሄር በተደራጁ ቡድኖች መካከል የሚካሄዱ ጠቦች ችግር አለ።



በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ተማሪዎች ህገ ወጥ አደንዛዥ ፅፆችን፣ ሽጉጥና ጠመንጃዎችን በማምጣት ችግር ይፈጥራሉ። በዚህ ምክኒያት አደጋ የተጋረጠባቸውና ፍርሀት ያደረባቸው ተማሪዎች፣ ችግር ፈጣሪዎቹን መጋፈጥ ትተው ስለሁኔታው ለመምህራቸው፣ ለትምህርት ቤቱ ካውንስለር ወይንም ደግሞ ለአስጠኚያቸው ማሳወቅ አለባቸው።

ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በልጆቻቸው የትምህርት ህይወት ጉልህ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል። የበቃ እንግሊዘኛ ባይናገሩም እንኳ የልጆቻቸውን ትምህርት ቤቶች እንዲጎበኙ፣ ከመምህራን ጋር እንዲተዋወቁና በትምህርት ቤት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ ይበረታታሉ። በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውሱን ለሆነ ወላጆች ኢንፎርሜሽን ይሰጣሉ። የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤቶች፣ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳሉ።

## የጎልማሶች ትምህርት

በርካታ አሜሪካውያን ትምህርት፣ የእድሜ ልክ ክንውን ነው ብለው ያምናሉ። ስለዚህም አብዛኞቹ አዋቂዎች ስራ እየሰሩ ትምህርት ቤት ይገባሉ። ስራቸውን ከኮጭራሹ አቋርጠው፣ ሙሉ ሰዓታቸውን ትምህርት ላይ ማዋል የሚችሉት ጥቂት ናቸው። አብዛኞቹ ስራ እየሰሩ ነው የሚማሩት።



አዲስ መጤዎች ስራ እንዲሰሩ የሚጠበቁ ቢሆንም ትምህርታቸውን መከታተል ይችላሉ። አብዛኞቹ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ይማራሉ፣ ሌሎች ደግሞ የሙያ ማሻሻያ ኮርሶች ይወስዳሉ። ለነገሩ የሚበዙት የሙያ ማሻሻያ ኮርሶች፣ ጥሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ይጠይቃሉ። እርስዎም ቢሆን አንዴ ተረጋግተው መኖር ከጀመሩ በኃላ ስለ ትምህርት ዕድሎች ግንዛቤ ያገኛሉ። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመጡበት በመጀመሪያው አመት ከፍተኛ ትምህርት የመቀጠል ዕድልዎ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ቀስ በቀስ ተምረው ዲግሪ ለመያዝ ወይንም ደግሞ በሙያዎ ለመስራት የሚያስችል ሰርቲፊኬት ማግኘት ይችላሉ። በቤተሰብ ውስጥ ስላለ አዋቂ ትምህርትም ሆነ ስለ ክፍያው ጉዳይ ለማቀድ፣ ቤተሰብ አንድ ላይ ቢመክርና ቢነጋገር ጠቃሚ ነው።

## እንግሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (ESL)

በርካታ ኮሚኒቲዎች በጎልማሶች የትምህርት ፕሮግራሞቻቸው አማካኝነት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቶች ያስተምራሉ። እነዚህ ትምህርቶች ሴትና ወንድ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ትውልድ ሳይል ለሁሉም ይሰጣሉ። ትምህርቶቹ በአብዛኛው የሚያተኩሩት በኮሚዩኒቲ ውስጥና በስራ ቦታ መግባባት እንዲቻል



ለማድረግ ነው። ለጀማሪዎች የሚሰጠው ትምህርት መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላትና ራስን ለማስቻል ነው። ለመካከለኛና ከዚያ በላይ ላሉት የሚሰጠው ትምህርት ደግሞ በሰዋሰው፣ በንባብና በፅሁፍ ላይ ያተኩራል።

በበጎ ፈቃድ አስጠኚ (ቱተር) መማር፣ እንግሊዘኛ ቋንቋን የመማሪያ ሌላው መንገድ ነው። ቋንቋን ብቻ ሳይሆን የአሜሪካንን ባህል ለማወቅ ጥሩ መንገድ ነው። ከጎልማሶች ትምህርት ቢሮ ወይንም ደግሞ ከማቋቋሚያ ድርጅት ሰራተኞች፣ ስለ በጎ ፈቃደኛ አስተማሪዎች ፕሮግራም ኢንፎርሜሽን ሊያገኙ ይችላሉ። ቋንቋ የሚያስተምሩ የግል ትምህርት ቤቶች አሉ ዳሩ ግን በአብዛኛው የሚያስከፍሉት ዋጋ ውድ ነው። እንግሊዘኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ ትምህርቶች ማለት ESL በተጨማሪ፣ የጎልማሶች ፕሮግራም የተለያዩ ኮርሶች ይሰጣሉ። ከእነዚህ መካከል የሂሳብ አያያዝ፣ የውጪ ቋንቋና የኮምፒውተር አጠቃቀም ይገኙበታል። አብዛኖቹ ኮርሶች እንግሊዘኛን በደንብ ለማይናገሩ ተማሪዎች የተቀየሱ አይደሉም። የጀነራል ኤዱኬሽን ዲቨሎፕመንት የGED ኮርሶች፣ አዋቂዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ እንዲያገኙ የሚረዱ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ ሰዎች የአሜሪካ ዜግነት እንዲያገኙ ያዘጋጃሉ። የጎልማሶች ትምህርት ለማግኘት ስደተኞች እንደ ማንኛውም ነዋሪ መክፈል አለባቸው።

## ሌሎች ስልጠናዎችና ከፍተኛ ትምህርት

አውቶሜካኒክ፣ ኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ፣ የጤናና የጥርስ ህክምና ረዳትነትን በመሳሰሉ የሙያ ዘርፎች የሚያሰለጥኑ ቮኬሽናልና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች አሉ። እነዚህ ስልጠናዎች በአብዛኛው ከፍተኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋ እውቀት እንዲሁም ክፍያ ይጠይቃሉ።

በዩናይትድ ስቴትስ ሁለት አይነት ከፍተኛ ትምህርቶች አሉ። እነርሱም መለስተኛ ወይንም ኮሚዩኒቲ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ወይንም ኮሌጆች ናቸው። የኮሚዩኒቲ ኮሌጆች ተማሪዎችን ለተወሰነ ማለትም የኤሌክትሮኒክ ጥገናና ነርስነት ለመሳሰሉ የሙያ ዘርፎች የሚያዘጋጁ፣ የሁለት አመት ትምህርት ይሰጣሉ። በኮሚዩኒቲ ኮሌጆች ሁለት አመት የተማሩ ተማሪዎች፣ አንድ አይነት የሙያ ብቃት ፈቃድ ወይንም ላይሰንስ ማግኘት ይችላሉ። አሊያም ደግሞ የሁለት አመት ትምህርታቸው፣ ለአራት አመት የኮሌጅና የዩኒቨርሲቲ ትምህርት መሸጋገሪያ ይሆንላቸዋል። ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የአራት ዓመት ትምህርት ይሰጣሉ። የኮሌጅ ተማሪዎች በፊዚክስ፣ በማቲማቲክስ፣ በታሪክ ወይንም ደግሞ ይበልጥ በትምህርት ገፍተው ህግና ህክምናን የመሳሰሉ የትምህርት አይነቶችን ከመከታተላቸው በፊት፤ አጠቃላይ ወይንም ጀነራል ኮርሶችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ይጠይቃሉ። እንግሊዘኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያልሆነ ተማሪዎች የቋንቋ ፈተና ተፈትነው ማለፍ አለባቸው።

"እንግሊዘኛን እንደ በር መክፈቻ ቁልፍ አድርጌ በመቁጠር ነው የተማርኩት። ወደ አንድ ቤት የሚያስገባው በር ከተቆለፈ ያለ ቁልፍ መግባት አይቻልም። እናም ታዲያ የዚህን ሀገር አካሄድ ለመረዳት እንግሊዘኛ ማወቅ ያስፈልጋል። እንግሊዘኛ ልክ እንደ አሜሪካ በር መክፈቻ ቁልፉ ነው ማለት ነው።"

ከፍተኛ ትምህርት ውድ ነው። አብዛኞች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ለትምህርት ክፍያ ስለሚሰጥ ብድርና ስለ ነፃ ትምህርት ዕድል ኢንፎርሜሽን የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎት ቢሮዎች አሏቸው።


ከሀገራቸው ህክምናንና ኢንጂነሪንግን በመሳሰሉ ሙያዎች ዲግሪ ይዘው የመጡ ሰዎች፣ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በነበራቸው ሙያ ለመቀጠል የሚያስችል የሙያ ብቃት ሰርቴፊኬት ማውጣት ይኖርባቸዋል። ይህ ሂደት ረጅም ጊዜ የሚወስድና ውድ ከመሆኑም በላይ፣ ከመጡበት ሀገር የትምህርትና የልምድ ብቃት ማረጋገጫ ማቅረብና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፈተናን ለማለፍ የሚያስፈልገውን ነጥብ ማሟላት ያስፈልጋል። ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሙያ መመለስ የሚፈልጉ ስደተኞች የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ለማግኘት ጥረት ላይ እያሉ፣ በአብዛኛው ከሙያው የተያያዘ፣ ነገር ግን ዝቅተኛ ስራ ይሰራሉ። ለምሳሌ ያህል አንድ ሀኪም በዩናይትድ ስቴትስ ለመስራት የሚያስችለውን ሰርተፊኬት እስከሚያገኝ ድረስ፣ በላቦራቶሪ ቴክኒሺያንነት ሊሰራ ይችላል።













THE AMERICAN UNIVERSITY
HEALTH INSURANCE CLAIM FORM
MAIL TO:



በዩናይትድ ስቴትስ የጤና እንክብካቤ ሲባል የተለያዩ አሰራሮችንና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል። በአካባቢዎ ያለን የጤና አገልግሎት በተመለከተ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን መረጃ መጠየቁ ይጠቅማል።

ዩናይትድ ስቴትስ እንደገቡ ብዙም ሳይቆዩ፣ እርስዎና ቤተሰብዎ **የጤና እክሎችን ሊከላከሉ የሚያስችሉ የጤና ምርመራዎች** እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ። የእነዚህ የጤና ምርመራዎች አላማ፣ ስራ መያዝ ወይንም ደግሞ ስልጠና ማግኘትን ጨምሮ የመቋቋም ሂደትዎን የሚያደናቅፍ የጤና ችግር ካለዎ ለማወቅና ለማከም ነው። የጤና ምርመራው ነፃ ሲሆን በህዝብ ጤና ቢሮ፣ በኮሚዩኒቲ የጤና ማዕከል ወይንም በዶክተሮች ክሊኒክ ሊከናወን ይችላል።

በዩናይትድ ስቴትስ ማንኛውም የህክምና ወጪ፣ በግለሰቦች እንጂ በመንግስት አይሸፈንም። የህክምና ወጪ ውድ በመሆኑ፣ በርካታ ሰዎች በጤና አገልግሎት ለመጠቀም፣ በአብዛኛው በአሰሪያቸው አማካኝነት በሚሰጡ የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች ላይ ይተማመናሉ።

**የጤና ኢንሹራንስ** በወርሀዊ ክፍያ ሊገኝ ይችላል። አንዳንድ አሰሪዎች ለሰራተኞቻቸው የጤና ኢንሹራንስ ክፍያን በከፊል ወይንም ደግሞ ሙሉ በሙሉ ይሸፍናሉ። አብዛኛውን ጊዜ አንድ አዲስ ተቀጣሪ፣ የጤና ኢንሹራንስ ከማግኘቱ በፊት ለተወሰነ ጊዜ መስራት ይጠበቅበታል። የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ በርካታ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች አሉ። ሄልዝ ሜንተናንስ ኦርጋናይዜሽንስ (HMO) የተባለው በጣሙን እየተለመደ የሄደ የጤና ኢንሹራንስ ፕሮግራም ነው። በዚህ ፕሮግራም የጤና አገልግሎት፣ በግል ሀኪሞችና ክሊኒኮች አማካኝነት ይሰጣል።

እያንዳንዱ የHMO አባል መሰረታዊ የጤና ህክምና የሚሰጠው ሀኪም ይኖረዋል። አንድ ታማሚ ወደ ድንገተኛ ህክምና ክፍልም ሆነ ወደ ሆስፒታል እንዲሄድ ወይንም ደግሞ ስፔሺያሊስት እንዲያይ ሀኪሙ መፍቀድ አለበት። በአንዳንድ ሁኔታዎች የህክምና ወጪዎች ሙሉ በሙሉ በኢንሹራንስ ይሸፈናሉ። በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ ታካሚም ወጪውን በከፊል እንዲሸፍን ይደረጋል።

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች የህክምና ወጪ የሚሸፍኑ፣ የፌደራል ፕሮግራሞች አሉ። ከዚህ በታች የተጠቀሱት እነዚህ የመንግስት ፕሮግራሞች፣ በየጊዜው ሊለዋወጡ ስለሚችሉ ወቅታዊ የሆነውን መረጃ ለማግኘት፣ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ሰራተኛ ይጠይቁ።

ስደተኞች፣ **ሬፌውጂ ሜዲካል አሲስታንስ** (RMA) በመባል የሚታወቀውን የስደተኖች ህክምና እገዛ ፕሮግራም ወይንም ደግሞ **ሜዲኬይድ** Medicaid ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ሁለቱም ፕሮግራሞች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች የህክምና ወጪ ይሸፍናሉ። አመልካቾች የገቢ ማረጋገጫና የግል ታሪካቸውን የሚጠይቁ ቅፆች መሙላት አለባቸው።

በእያንዳንዱ ኮሚኒቲ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች የተለያዩ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ የጤና ምርመራ፣ የጥርስ ህክምናና የአዕምሮ ጤና አገልግሎት ለማግኘት ቀጠሮ መያዝ ያስፈልጋል። በአካባቢዎ ምን አይነት የጤና አገልግሎቶች መኖራቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው። አንዳንዶቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

**ፓብሊክ ሄልዝ ዲፓርትመንት፣** እነዚህ ማዕከላት ክትባቶችንና የጤና ችግሮችን መከላከል የሚያስችሉ ምርመራዎች ይሰጣሉ። ይህም የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምርመራንና ህክምናን ይጨምራል።



እነዚህ አገልግሎቶች ለስደተኞች በነፃ ወይንም ደግሞ በጣም በዝቅተኛ ክፍያ ይሰጣሉ። ወላጆች ወደ እነዚህ የጤና ማዕከላት ሄደው ስለ ልጆቻቸው ክትባት ጉዳይ ማነጋገር ይኖርባቸዋል። መንግስት ትምህርት ቤቶች የሚገቡ ልጆች በሙሉ፣ አስፈላጊ ክትባቶች መውሰዳቸውን የሚያመለክት ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

**የግል ሀኪሞች** እነዚህ አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ወይንም ደግሞ በተለየ የህክምና ዘርፍ አገልግሎት ይሰጣሉ። የግል ሀኪሞች፣ ታካሚው ለሚያገኘው አገልግሎት የመክፈል አቅም ወይንም ደግሞ ኢንሹራንስ እንዳለው፣ በቀጠሮው ሰዓት ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። አንዳንድ ሀኪሞች የግል ክሊኒክ አባል ወይንም የአጠቃላይ ጤና ሀኪሞችም ሆነ የስፔሺያሊስቶች ቡድን አካል ሆነው ነው የሚሰሩት።

**የኮሚዩኒቲ ክሊኒኮች ወይንም የጤና ማዕከላት**
በመንግስትና በግለሰቦች ድጋፍና እርዳታ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። የግል ኢንሹራንስ ወይንም ሜዲኬድ የሚቀበሉ ሲሆን፣ ታካሚው ኢንሹራንስ ከሌለው በገቢው መጠን ተመጣጣኝ ክፍያ ያስከፍላሉ።

**ሆስፒታሎች** በእያንዳንዱ የአሜሪካ ኮሚዩኒቲ ይገኛሉ። ሀኪሞችና ክሊኒኮች የተለየ ችግር ያለባቸውን ህሙማን፣ ለምርመራና ለቀዶ ህክምና ወደ ሆስፒታሎች ይልካሉ። የሆስፒታል ህክምና አገልግሎቶች ውድ በመሆናቸው፣ ታካሚው የመክፈል አቅም ያለው መሆኑንና ወይንም ወጪው በኢንሹራንስ ይሸፍን እንደሁ ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ።

**ድንገተኛ ክፍሎች** በሆስፒታሎችና በሌሎች የህክምና ተቋማት የሚገኙ ሲሆን፣ ለድንገተኛና ለፅኑ የጤና ችግር አገልግሎት ይሰጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ ድንገተኛ ክፍሎች በህሙማን የተጣበቡ ናቸው። ቀጠሮ ስለማያስፈልጋቸውም ወረፋቸው ረጅም ነው። ለአብዛኛው የጤና ችግርዎ ሀኪም ጋር ቀጠሮ መያዝ አለብዎት። ወደ ድንገተኛ ክፍል የሚሄዱት በጣሙን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ይሁን። አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው ኢንሹራንስ ወይንም ደግሞ የመክፈል አቅም ኖረው አልኖረው፣ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ያገኛል።

**የአምቡላንስ አገልግሎት** ይህ አገልግሎት በፅኑ የታመመ ወይንም አደጋ የደረሰበት ሰው፣ አስቸኳይ የጤና እርዳታ ወደሚያገኝበት ስፍራ ያደርሳል፣ ጊዜያዊ እርዳታም ይሰጣል። አብዛኛውን ጊዜ ለአንቡላንስ አገልግሎት ክፍያ የሚጠየቀው፣ አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ ነው።

**የጥርስ ህክምና** በግል የጥርስ ሀኪሞችና ክሊኒኮች ይሰጣል። ነፃ ወይንም ርካሽ የጥርስ ህክምና አገልግሎት ማግኘት አዳጋች ቢሆንም፣ በፓብሊክ ሄልዝ ዲፓርትመንቶችና በኮሚዩኒቲ የጤና ማዕከላት በኩል ሊገኝ ይችላል። ሁሉም የጤና ኢንሹራንሶች፣ በፕሮግራሞቻቸው የጥርስ ህክምና አገልግሎትን አያካትቱም።

**የአእምሮ ጤና እንክብካቤ** ይህ አገልግሎት በግል ሀኪሞች፣ ክሊኒኮች ወይንም ቴራፒስቶች ይሰጣል። አንዳንድ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ሚዩችዋል አሲስታንስ አሶሲየሽንስ ተብለው በሚጠሩት፣ የጋራ መረዳጃ ድርጅቶችና በቤተሰብ አገልግሎት አማካኝነት ይሰጣሉ። አንዳንድ የማቋቋሚያ ድርጅቶች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፣ ሌሎች የአዕምሮ ጤና እንክብካቤ ሰጪዎችን ለማግኘትም ይረዳሉ።




SALE


Mellon Bank
24 Hour Banking






Preferred
SHOPPER
AMERICAN EXPRESS

በዩናይትድ ስቴትስ ኑሮ በአመዛኙ ውድ ነው፣ ስለዚህም ስደተኞች ስለ በጀት ምደባ፣ ስለ ገንዘብ ቁጠባና ስለ ክሬዲት ማለት ዱቤና ብድር አጠቃቀም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

## የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም

በተወሰነ ገቢ ሲኖር፣ ስለ ገንዘብ አያያዝ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። መሰረታዊ ወጪዎች የሚባሉት ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው።

**የቤት ኪራይ** ትልቁ ወጪዎ ሲሆን፣ በጀት ሲያወጡ የመጀመሪያው ጉዳይ የሚያደርጉት መሆን አለበት።

**ዩቲሊቲ** ለኤሌክትሪክ ሊጋዝ፣ ለውሀና ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚወጣ ክፍያ ነው። አንዳንድ ጊዜ ዩቲሊቲ ከቤት ኪራይ ጋር ተጠቃሎ ይመጣል፣ አለዚያ ደግሞ ለብቻው የሚከፈል ይሆናል። የቤት ማሞቂያና ማቀዝቀዣ ወጪ እንደ አየር ፀባዩ ሁኔታ ይቀያየራል።

**ምግብ** በተቻለ መጠን የሸቀጦች ዋጋ ዝቅተኛ በሆነባቸው ታላላቅ ሱቆች ይገብዩ። ዋጋ ያወዳድሩና፣ ቀነስ ያለውን አይነት መርጠው ይግዙ።

**ትራንስፖርት** በየቀኑ ከቤት ወደ ስራ የሚመላለሱበትን፣ ወደ ሱቅና ወደ ሌሎች ቦታዎች የሚጓዙበት ወጪ መመደብ አለብዎት። በበርካታ አካባቢዎች ለአውቶቡስና ሆነ ለባቡር መጓጓዣ የሚሆኑ ወርሀዊ ቅናሽ ትኬቶች ይኖራሉ።

**ቴሌፎን** ከሚኖሩበት ከተማ ውጪ የሚደረግ ጥሪ ውድ መሆኑን ልብ ይበሉ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ የረጅም ርቀት ጥሪዎች ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም ሌሊት ላይ ይረክሳሉ።





"ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመጣሁ ከጥቂት አመታት በኋላ፣ መኪና የምገዛበት ወቅቱ ደርሷል ብዬ ወሰንኩ። ወደ መኪና ሻጭ ሄጄ ብድር ለማግኘት የሚፈቅደውን ሰው ስጠይቅ ከዚህ ቀደም ተበድሬ እንደሁ ጠየቀኝ።

አዎን ብዬ ከIOM የወሰድኩትንና የከፈልኩትን ብድር አሳየሁ። ብድር ወስጄ መክፈል መቻሌን ስላረጋገጥሁ፤ ያቀረብኩት የብድር ጥያቄ ተፈቀደልኝ።"






## የትኛው ገበያ ይሻላል?

በዩናይትድ ስቴትስ የተለያዩ የገበያ አዳራሾችና ሱቆች አሉ። በዛው ልክ የሚያቀርቧቸው ሸቀጦችም ሆነ አገልግሎቶች እንዲሁ በጣም ይለያያሉ። በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ አምስት አይነት ገበያዎች ወይንም ሱቆች ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው።

**ሱፐር ማርኬቶች** በጣም የተለመዱ የምግብ መሸጫ መደብሮች ናቸው። ከምግብ ሸቀጦች ሌላ የፅዳት መጠበቂያ ምርቶች፣ ቅባቶችና የውበት መጠበቂያ ውጤቶች ኮስሜቲክስ፣ መፅሄቶች አንዳንድ ልብሶችና የቤት እቃዎች እንዲሁም የሀኪም ትዕዛዝ የማያስፈልጋቸው መድሀኒቶች ይሸጣሉ። በርካታ ሰዎች በኩፖኖች በመጠቀም ቅናሽ ያገኛሉ፣ እንዲሁም ሱፐር ማርኬቶች በስማቸው የሚያመርቷቸውን ሸቀጦች ወይንም ደግሞ ለጊዜው ቅናሽ ላይ የወጡ ሸቀጦችን በመሸመት ወጪያቸውን ይቀንሳሉ።

**ዲፓርትመንት ስቶር** እነዚህ መደብሮች ልብሶች፣ የቤት እቃዎች፣ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እንደ ማቀዝቀዣና ማብሰያ የመሳሰሉ ቁሳቁሶች፣ ጫማዎችና ሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ይሸጣሉ። አንዳንዶቹ ዲፓርትመንት ሱቆች ዋጋቸው ረከስ ያለ ሸቀጦች ያቀርባሉ።

**የአሮጌ እቃ መደብሮች (ትሪፍት ሾፕስ)** እነዚህ ሱቆች አሮጌ እቃዎችን በመጠነኛ ዋጋ ያቀርባሉ። ብዙ ሰዎች ወደ እነዚህ ሱቆች ጎራ እያሉ፣ በርካሽ ዋጋ እቃ መግዛታቸውን በኩራት ይናገራሉ።

**የብሄረሰብ ምግብ መሸጫ መደብሮች** እነዚህ የምግብ መሸጫ መደብሮች አብዛኛውን ጊዜ በቀድሞ ስደተኞችና ኢሚግራንቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ ሱቆች በአብዛኛው ኮሚዩኒቲ ወይንም በአቅራቢያዎ ከተማ

በርካታ መጤዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ይገኛሉ። በእነዚህ አይነት ሱቆች በአገርዎ የለመዷቸውን የምግብ አይነቶች ያገኛሉ።

**ያርድ ሴል ወይንም ጋራዥ ሴል** እንደ በረንዳ ሽያጭ አይነት ሲሆን በጋዜጦች ወይንም በተተከሉ የፅሁፍ ማስታወቂያዎች ይከናወናል። በእነዚህ አይነት ገበያዎች ሰዎች ማስታወቂያ እያወጡ የቤት እቃዎቻቸውን በጣም በርካሽ ዋጋ ይሸጣሉ። የቤት ቁሳቁሶችንና ልብሶችን ለመግዛት የሚመረጡ ገበያዎች ናቸው።

## የሽያጭ ታክስ

በብዙ ስቴቶች ሸማቾች በሚገዙት እቃ ላይ የሽያጭ ታክስ መክፈል አለባቸው። አንዳንድ ነገሮች ማለት ምግብና መድሀኒት ከታክስ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ታክስ በእቃ ዋጋ ላይ በመቶኛ ተባዝቶ ግዢው ሲከናወን በካሽ ሬጂስተሩ ላይ የሚሰላ ነው። በአንድ ዕቃ ላይ የተለጠፈ ዋጋ በአብዛኛው የሽያጭ ታክሱን አይጨምርም።

## ሌሎች ታክሶች

ፌደራልና ስቴት እንዲሁም አንዳንድ የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ታክስ ይሰበስባሉ። ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የአካባቢ አስተዳደሮች በቤት፣ በህንፃ፣ በመሬትና አንዳንዴም መኪናዎችን በመሳሰሉት ላይ የንብረት ታክስ ያስከፍላሉ። እነዚህ ታክሶች ስደተኞችን ጨምሮ ሁሉም ነዋሪ ተጠቃሚ ለሚሆንባቸው አገልግሎቶች ይውላሉ።

## የባንክ አገልግሎት

በርካታ አሜሪካውያን ገንዘባቸውን ለመጠበቅና ከስርቆት ለማዳን፣ ገንዘባቸውን ከመኖሪያ ቤታቸውን ይልቅ ባንክን፣ የቁጠባና ብድር ማህበራትን በመሳሰሉ የገንዘብ ተቋማት ውስጥ ያስቀምጣሉ። እነዚህ የገንዘብ ተቋማት በአብዛኛው ለተቀማጭ ገንዘብ ወለድ የሚከፍሉ ሲሆን ለቼክ ሂሳብና

የቼክ ሂሳብና ብድርን ለመሳሰሉ አገልግሎቶች ያስከፍላሉ። በርካታ ሰዎች ቢል ማለት ወጪዎቻቸውን ለመክፈል ቼክ የሚፅፉበት አካውንት ወይንም የባንክ ሂሳብ አላቸው።

## የክሬዲት አጠቃቀም

በዩናይትድ ስቴትስ በክሬዲት ማለት በዱቤ ካርድ እቃም ሆነ አገልግሎት መግዛት የተለመደ ነገር ነው። ይህ ማለት እቃ ከተገዛ ወይንም አገልግሎት ከተሰጠ በኃላ፣ ክፍያው ወዲያውኑ ሳይሆን ቆይቶ ይፈፀማል፣ በዱቤ መግዛት ማለት ነው። በርካታ ነጋዴዎች፣ ሸቀጣቸውንና አገልግሎታቸውን ገዝተው ለመጠቀም አቅሙ ለሌላቸው ሰዎች፣ በክሬዲት እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ። አዲስ መጤዎች፣ እንደ ቤት እቃዎችና መኪኖችን የመሳሰሉ ነገሮችን ለመግዛት በክሬዲት ካርድም ሆነ በክሬዲት እቅድ ለመጠቀም ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። በእቃዎቹ ዋጋ ላይ የወለድ ሂሳብ ስለሚጨመርበት አጠቃላይ ክፍያው በጣሙን ከፍ ይላል። በዚህ አይነት ዕቃ የገዛ ሰው ክፍያ ቢያልፍበት፣ ሻጩ ኩባንያ ቀደም ብሎ የከፈለውን ሂሳብ ሳይመልስ እቃውን መልሶ መውሰድ ይችላል። ችግሩ ይህ ብቻ አይሆንም፣ ገዢው የክሬዲት ሬኮርዱ ስለሚበላሽ ወደፊት ሌላ ክሬዲትም ሆነ ብድር ለማግኘት ይቸገራል። ከዚህ በተጨማሪ የዕውነት መሆኑን ለማመን ከሚያዳግት ወይንም እጅግ ከሚማርክ የክሬዲት ማስታወቂያ መጠንቀቅ ይጠቅማል።

ስደተኞች፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመምጣት ለመጓጓዣ የተበደሩትን ገንዘብ መልሰው ለመክፈል፣ ከገቢያቸው ገንዘብ መመደብ አለባቸው። ይህም ጥሩ የክሬዲት ታሪክ ለመመስረት ይጠቅማል። በዚህ አይነት አንዴ የተበደሩትን ገንዘብ መክፈል ከተቻለ፣ ሌላ ብድር ለመውሰድ ይቀላል። ወዲህ የመጡበትን የመጓጓዣ ገንዘብ መልሰው መክፈል ስለሚችሉበት መንገድ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ይጠይቁ።


This facility is
smoke free.
No Smoking









## መሸጋገሪያ የማቋቋሚያ አገልግሎቶች፣ ማስታወሻ

"የማቋቋሚያ ድርጅት ሚና" በሚል ርዕስ ገፅ 17 ላይ የተብራራው ቁም ነገር፣ ወዲህ ሲመጡ ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ ማግኘት የሚገባዎን ነገር ይዘረዝራል። ለአጭር ጊዜ የሚሰጡዎትን እነዚህ አገልግሎቶች በተቻለዎ መጠን የመጠቀሙ ሀላፊነት የእርስዎ ነው። ራስዎን በመቻል ሂደትዎ ያሳዩትን መሻሻል ምን ጊዜም ቢሆን ለማቋቋሚያ ድርጅትዎ ያካፍሉ። ስለ ፍላጎትዎና ስለ ስጋትዎ በግልፅ ያወያዩዋቸው፣ ግትር አይሁኑ።

"ስራ"ን በተመለከተ ገፅ 37 በሰራተኛነት ያለብዎትን ሀላፊነት ይዘረዝራል። ምንም እንኳ የመጀመሪያ ስራዎ የሙያ እርካታ ባይሰጥዎትም፣ የስራ አፈፃፀምዎ የወደፊት አሰሪዎችዎ ከግምት የሚያስገቡት ይሆናል። ስለዚህም በተቻለዎ መጠን ተግተው ለመስራት መጣሩ ወሳኝ ነው።

"ትምህርት"ን በተመለከተ ገፅ 53 ወላጆች ትምህርት ቤት የገቡ ልጆቻቸውን በተመለከተ ያለባቸውን ሀላፊነት ይዘረዝራል። በልጅዎ የትምህርት ሂደት ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ።

## የዩናይትድ ስቴትስ ህጎች

በስደተኛነትዎ፣ አሜሪካ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው ካሉት መብቶች አብዛኞቹ ይኖርዎታል። የዩናይትድ ስቴትስ ነዋሪ የሆነ ሰው ሁሉ የዘር፣ የፆታ፣ የሀይማኖት፣ የጎሳ፣ የትውልድ ሀገርና ሌሎች ልዩነቶች ሳይደረጉበት ስራ መቀጠር፣ መኖሪያ ቤት ማግኘት፣ መማርና የመንግስት አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው። የዩናይትድ ስቴትስ ህጎች፣ መብትዎን ለማስከበር ታስበው የተቀረፁ ናቸው። እንደ ዩናይትድ ስቴትስ ነዋሪነትዎ ስለ ህጋዊ መብቶችዎና ግዴታዎችዎ መሰረታዊ እውቀት ሊኖርዎት ይገባል።



በዩናይትድ ስቴትስ በወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት ቢቀርቡ፣ ጥፋተኝነትዎ በፍርድ ቤት እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሰው ተደርገው ይቆጠራሉ። የሚከራከርልዎ ጠበቃ የማቆም መብት አለዎት። ጠበቃ ለመቅጠር አቅም ከሌለዎት ደግሞ ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ያቆምልዎታል። ዳሩ ግን ህግ ጥሰው ቢገኙ የሚገጥምዎትን ችግር፣ የማቋቋሚያ ድርጅቱ ጣልቃ ገብቶ ሊፈታ አይችልም።

## ከሀገርዎ ህጎች ሊለዩ የሚችሉ የዩናይትድ ስቴትስ ህጎች

- ብዙ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ለምሳሌ እንደ ቲያትር ቤቶችና ቢሮዎች ባሉ ስፍራዎች፣ ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው። በሌሎች ስፍራዎች ማለት እንደ ምግብ ቤትና ቡና ቤት ባሉ ቦታዎች፣ ለአጫሾች በተለየ የተዘጋጀ ስፍራ ይኖራል። ለማንኛውም አጫሽ ከሆኑ፣ በአካባቢዎ ስላለው ህግ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ይጠይቁ።
- ናርኮቲክስ ማለት አደንዛዥ እፆችን መግዛትና መሸጥ ክልክል ነው። በሀገርዎ ህጋዊ የሆኑ ዳሩ ግን በዩናይትድ ስቴትስ ህገ ወጥ የሆኑ እፆችን በተመለከተ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ጠይቀው ይረዱ።
- የዩናይትድ ስቴትስ መንጃ ፈቃድ ሳይኖርዎት ወይንም ደግሞ አልኮል ጠጥተው፣ መኪና መንዳት ክልክል ነው።



- በበርካታ ስቴቶች ልጆች መኪና ላይ ሲሳፈሩ፣ ደህንነታቸውን አስመልክቶ የወጡ ህጎች አሉ። ለምሳሌ ልጆች በሲት ቤልት ማለት በቀበቶ መታሰር አለባቸው፣ ህፃናት ደግሞ የተለየ መቀመጫ ሊደረግላቸው ይገባል። አዋቂዎችም እንዲሁ ሲት ቤልት ይሰሩ የሚል ተመሳሳይ ነህግ አለ።
- ባለቤትዎን ወይንም ልጆችዎን መደብደብ ህገ ወጥ ድርጊት ነው።
- ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ካልደረሱ (18 ዓመት ካልሞላቸው) ልጆች ጋር የወሲብ ግንኙነት መፈፀም ክልክል ነው።
- በስራ ቦታ ሰውን የሚያስቀይሙ አስተያየቶች መሰንዘርና ወሲባዊ ባህሪይ ማሳየት (ሴክሽዋል ሀራስመንት) ክልክል ነው።
- እድሜያቸው ከ18-35 የሆነ ወንድ ስደተኞች፣ በጦርነት ጊዜ ግለሰቦችን ለወታደራዊ ግዳጅ ለሚጠራውና ሰሌክቲቭ ሰርቪስ በተባለው የመንግስት መስሪያ ቤት መመዝገብ አለባቸው። በአሁኑ ወቅት የዩናይትድ ስቴትስ የጦር ሀይሎች አባላት በሙሉ በፈቃደኝነት የተመለመሉ ናቸው።
- በበርካታ ስፍራዎች፣ ፍቃድ ሳይኖር ማደንና አሳ ማጥመድ ክልክል ነው። ከአደንና ከአሳ ማስገር ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ የወጡ ህጎችን ማወቅና ማክበር አለብዎት።

## ህጋዊ ነዋሪነትና ዜግነት

በስደተኛነት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መምጣትዎ፣ ቋሚ ነዋሪ በኃላም ደግሞ የአሜሪካ ዜጋ እንዲሆኑ መንገድ ይከፍታል። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመጡ በመጀመሪያው አመት፣ እንደ ስደተኛ ይቆጠራሉ። በዚህ ወቅት ህጋዊ ነዋሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ ሁል ጊዜ የI-94 ካርድዎን ኮፒ ወይንም ቅጂ መያዙ ይመረጣል። እንደ ስደተኛ በሚቆጠሩበት ጊዜ፣

- በየትኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ግዛት መዘዋወር
- ንብረት መግዛት
- ስራ መቀጠር
- ትምህርት ቤት መግባት
- የተለዩዎትን ባለቤትዎንና ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችዎን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ማስመጣት ይችላሉ። ባለቤትዎንና ልጆችዎን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ማምጣት ከፈለጉ፣ ምን ምን ነገሮች ማሟላት እንደሚገባዎ ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ ሰራተኛ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

በዩናይትድ ስቴትስ መሰረታዊዎቹ የመናገር፣ የሀይማኖትና የመሰብሰብ ነፃነቶች፤ ስደተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ሰው የተረጋገጡ መብቶች ናቸው። አንዳንድ የማቋቋሚያ ድርጅቶች ከሀይማኖት ቡድኖች ጋር ግንኙነት ቢኖራቸውም ቅሉ፣ በእነርሱ የሀይማኖት እንቅስቃሴ ውስጥ የመሳተፍ አንዳችም ግዴታ የለብዎትም።

በስደተኛነት ወይንም በሬፊውጂነት በሚኖሩበት ጊዜ የአሜሪካ ፖስፖርት መያዝ፣ የጦር ሀይሎች አባል መሆን፣ በአሜሪካ ምርጫዎች ድምፅ መስጠትና ዜጋ መሆንን በሚጠይቁ የመንግስት ስራዎች መቀጠር አይችሉም። ከዜግነትና ኢሚግሬሽን አገልግሎት CIS ፍቃድ ሳያገኙም ከዩናይትድ ስቴትስ መውጣት አይችሉም። ወደ ውጪ ሀገር መሄድ ቢፈለጉ፣ የጉዞ ፈቃድ ያገኙ ዘንድ ምን

ማድረግ እንዳለብዎት የማቋቋሚያ ድርጅትዎ ያስረዳዎታል። በስደተኛነት እያሉ ወደ ትውልድ ሀገርዎ ቢመለሱ፣ ስደተኛነትዎን ለአደጋ ከማጋለጡም በላይ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ተመልሰው እንዳይገቡ ሊከለከሉ ይችላሉ።

በዩናይትድ ስቴትስ ለአንድ አመት ከኖሩ በኃላ፣ ቋሚ ነዋሪ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ። ከአንድ አመት በላይ መቆየት የለባቸውም እንጂ፣ ቋሚ ነዋሪዎች ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ መጓዝ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ጦር ሀይሎች አባል መሆን ይችላሉ። ዳሩ ግን በዩናይትድ ስቴትስ ምርጫዎች ድምፅ መስጠት፣ ለውጪ መንግስታት መስራትና ዜጋ መሆንን የሚጠይቁ የመንግስት ስራዎች መያዝ አይችሉም። የማቋቋሚያ ድርጅትዎ፣ እንዴት አድርገው ቋሚ ነዋሪ መሆን እንደሚችሉ ማብራሪያ ይሰጥዎታል።

በዩናይትድ ስቴትሰ ለአራት አመታት ተከታትለው ከኖሩ በኃላ ዜጋ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ። ለዜግነት የሚያበቁ መመዘኛዎች ምን ምን እንደሆኑ ከዜግነትና ኢሚግሬሽን አገልግሎት ከCIS ወይንም ከማቋቋሚያ ድርጅትዎ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። ከመመዘኛዎቹ መካከል ጥሩ ስነምግባር፣ መሰረታዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ እንዲሁም ስለ ዩናይትድ ስቴትስ ታሪክና መንግስት ማወቅ ይገኙበታል። የአሜሪካ ዜግነት የወሰዱ ሰዎች፣ ልክ እዚህ ሀገር እንደተወለዱ ዜጋዎች ሁሉ እኩል መብት አላቸው።









ዩናይትድ ስቴትስ፣ የተለያዩ ባህሎችንና ልምዶችን ይዘው የመጡ ኢሚግራንቶች ሀገር ናት። ይህ ልዩ የሆነ ስብጥር፣ አንድ ወጥ የሆነ የአሜሪካ ባህል አለመኖሩን ያመለክታል። የሆነ ሆኖ በዩናይትድ ስቴትስ ከመጡበት ሀገር የተለዩ ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ባህሎች፣ ወጎችና አመለካከቶች አሉ። ጥቂቶቹም እንግዳ፣ እንደውም ከራስዎ ባህሎች ጋር ሊጋጩ ይችላሉ። እነዚህን የአሜሪካውያን ባህሎችና እሴቶች የማወቅና የመለማመድ ሂደት፣ ከባህሉ ለመዋሀድ የሚያደርጉት ጥረት አካል ነው። ጥረቶች ማድረግ ማለት የራስን ባህል እርግፍ አድርጎ መተው ማለት አይደለም።

አሜሪካውያን በሰዎች እኩልነት ያምናሉ። ዘር፣ ሀይማኖት፣ ፆታና ትውልድ ሳይል የሁሉም ሰው ሰብዓዊ መብት እንዲከበር ይፈልጋሉ። አሜሪካውያን በአብዛኛው፣ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሰዎች ላይ አድልዎ በሚፈፅሙ ሰዎች ላይ ጥሩ አመለካከት የላቸውም። ዘር፣ ሀይማኖት ወይንም ጎሳን መሰረት በማድረግ በስራ ቦታም ሆነ ቤት ከማከራየት ጋር በተያያዘ አድልዎ እንዳይፈፀምብዎ የሚከለክሉ ጥብቅ ህጎች አሉ።

በዩናይትድ ስቴትስ የሴቶችና የወንዶች ሚና እርስዎ ከመጡበት ሀገር የተለየ ሊሆን ይችላል። አሜሪካውያን በፆታ እኩልነት ያምናሉ፣ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ራስን በመቻል ከጥገኝነት መውጣት አለባቸው ይላሉ። በቤተሰብዎ የእርስዎና የባለቤትዎ ሚና ሊለወጥ ይችላል፣ ዳሩ ግን ይህን ሁኔታ የመልሶ መቋቋም ሂደት አካል አድርገው ይቁጠሩት። አብዛኛውን ጊዜ የቤተሰብን መሰረታዊ የቤት ወጪ ለመሸፈን፣ ከአንድ ገቢ በላይ ሊያስፈልግ ይችላል። በዚህ የተነሳ ባልና ሚስት ሁለቱም ስራ መስራት የግድ ስለሚሆንባቸው፣ የልጆችን ሀላፊነት እኩል መጋራት ይኖርባቸዋል።



በዩናይትድ ስቴትስ፣ በቤተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ህጎች አሉ። ከእነዚህም መካከል የሴቶችንና የልጆችን መብት የሚመለከት ይገኝበታል። ለምሳሌ ባለቤትዎንም ሆነ ልጆችዎን መደብደብ በህግ የተከለከለ ነው። ልጆችን በሚገባ ተንከባክቦ አለማሳደግ ከችላ ባይነት ያስቆጥራል፣ የህፃናት ተንከባካቢ ድርጅትን ጣልቃ ገብነት ሊያስከትል ይችላል።

ስለ አሜሪካ ህይወት በርካታ የተሳሳቱ አመለካከቶችና ግምቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ የሚሆነው በርካታ ፊልሞችና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ስለ ዩናይትድ ስቴትስ አኗኗር ሚዛን የጠበቀ መልዕክት ስለማያሰራጩ ነው። ከማስተማር ይልቅ ማዝናናት ላይ የሚያተኩሩት የመገናኛ ብዙሀን፣ አብዛኛውን ጊዜ የአሜሪካንን እሴቶች፣ አመለካከቶችና እውነታ አንፀባራቂ ዝግጅቶች አያቀርቡም። ወደ ዩናይትድ ስቴትሰ የሚመጡ ሰዎች በሙሉ፣ በጥቂቱም ቢሆን ስለ ዩናይትድ ስቴትሰ የተሳሳተ አመለካከት አላቸው። በተቻለ መጠን አስተዋይ ለመሆንና ለውጥን ለመቀበል ይጣሩ። ይህን ለማድረግ ጥሩ ጅማሮ የሚሆነው፣ ስላልገባዎ ወይንም ግር ስላለዎት ጉዳይ ጥያቄ መጠየቅ ነው።



## የባህል ለውጥ ችግርን ስለመቋቋም

የባህል ለውጥ ችግር፣ አንድ ሰው በማያውቀው ሀገር ቋንቋውን ሳይናገርና ባህሉን ሳይረዳ ሲቀር የሚሰማው የተስፋ መቁረጥና የብስጭት ስሜት ነው። ወደ አዲስ ሀገር ለመኖር የሚሄድ ማንኛውም ሰው፣ መጠኑ ይለያይ እንጂ ይህ ችግር ይገጥመዋል። ምልክቶቹም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፤

- ወደ ገበያ መሄድና ትራንስፖርት መያዝን የመሳሰሉ የዕለት ተዕለት ተግባራት ማከናወን አለመቻል
- በሌሊት እንቅልፍ ማጣትና በቀን መድከም
- ነጭናጫና ቁጡ መሆን
- የምግብ ፍላጎት መቀነስና ግድ የለሽነት

እነዚህ ስሜቶች በአብዛኛው ጊዜያዊ ሲሆኑ ቀስ በቀስ ይቀንሳሉ። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚመጡ በርካታ ሰዎች በእነዚህ ስሜቶች ውስጥ የሚያልፉ ሲሆን፣ ይበልጥ እየተቋቋሚቸው በሄዱ ቁጥር ይጠነክራሉ። የባህል ለውጥ ችግርን የመቋቋሚያው መንገድ እንደ ግለሰቡና እንደ ባህሉ ይለያያል። ወደሚወዱት ጊዜ ማሳለፊያ መመለስ አሊያም ደግሞ ሙዚቃ መስማት ሊረዳ ይችላል። አዲስ መጤዎች በሙሉ ለማለት ይቻላል የሚጠቀሙበት አንዱ ዘዴ፣



ከሚያውቋቸው የሀገር ልጆች ስብስብ ወይንም ከብሄረሰብ ቡድኖች ጋር መቀላቀል ነው።

አዲስ ህይወት ለመገንባት፣ ትዕግስትኛ መሆንና ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል። ቀኖችዎ በስራ ሊጣበቡ ይችላሉ ነገር ግን ይበልጥ ሲንቀሳቀሱና ህይወትዎን ለመምራት ተጨማሪ ሀላፊነት ሲወስዱ፣ የመልሶ መቋቋም ሂደትዎ ስኬታማ ይሆናል።

## ለዕለት ተዕለት ኑሮ ጠቃሚ ምክሮች

**ወግ አለማጥበቅ** (ኢንፎርማሊቲ) አሜሪካውያን ወግ አያጠብቁም። በማህበራዊ ግንኙነቶች ወቅት አቶ፣ ወይዘሮ ወይንም ወይዘሪት ከመባል ይልቅ በአብዛኛው በመጀመሪያ ስማቸው መጠራት ይመርጣሉ። በስራና በንግድ ግንኙነት ወቅት ደግሞ በተለይ ገና በትውውቅ ደረጃ እያሉ በቤተሰብ ስም (የአባት ስም እንደማለት ነው) ይጠቀማሉ። በርካታ አለቆችና የስራ ባልደረቦች በመጀመሪያ ስማቸው መጠራት ይመርጣሉ። "ዶክተር" ወይንም ደግሞ "ፒ ኤች ዲ"ን የመሳሰሉ የሙያ መጠሪያዎች በአብዛኛው አገልግሎት ላይ የሚውሉት፣ በተራ ግንኙነት ሳይሆን ስብሰባን በመሰሉ አጋጣሚዎች ነው። ከጓደኛዎ ሲገናኙም ሆነ አዲስ ሰው ሲተዋወቁ፣ ፈገግታ የተመላበትን ፊት ማሳየት በጣም ጠቃሚ ነው።

**ሰዓት ማክበር** ጊዜ ትልቅ ዋጋ አለው። አሜሪካውያን በተቻላቸው ሰዓት ለማክበር ይሞክራሉ፣ ሌሎችም እንዲሁ እንዲያከብሩ ይጠብቃሉ። በግልም ሆነ በስራ ህይወት ሰዓት ማክበር አስፈላጊ ነው። ቀጠሮ ሳይዙ ወደ አንድ መስሪያ ቤት ሄደው ጉዳይ ለማስፈፀም ቢሞክሩ፣ ላይሳካልዎ ወይንም የሚያነጋግርዎ ሰው ላይኖር ይችላል። በቀጠሮ ሰዓት መገኘት የማይችሉና ወይንም ደግሞ ከ15 ደቂቃ በላይ የሚያረፍዱ ከሆነ፣ ስልክ ደውለው ምክኒያትዎን ማስረዳት ያስፈልጋል።

**የግል ህይወት** አሜሪካውያን ወግ አጥባቂ ያልሆነ የአኗኗር ዘይቤ ቢከተሉም ቅሉ፣ ለግል ህይወታቸው ወይንም ለኑሮአቸው ትልቅ ግምት ይሰጣሉ። ሳይጋበዙ ወይንም በቅድሚያ ሳያስታውቁ ሰው ቤት ሄዶ መጠየቅ የተለመደ ነገር አይደለም። ገንዘብ ነክ ጉዳዮች የግል ተደርገው ይቆጠራሉ። አንድ ሰው ስንት ገቢ እንዳለው፣ መኪናውን ቤቱንም ሆነ ሌሎች ንብረቶቹን ስንት እንደገዛ መጠየቅ ነውር ነው። የማያውቁትንም ሆነ ገና የተዋወቁትን ሰው የግል ጥያቄ መጠየቅም እንዲሁ ነውር ነው።

**የግል ንፅህና** አብዛኞች አሜሪካውያን በየቀኑ ገላቸውንና ፀጉራቸውን ይታጠባሉ። ጥርሳቸውንም አዘውትረው ይቦርሻሉ። ልብሳቸውንም በየጊዜው ይቀይራሉ። የግል ንፅህናን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምርቶች አሉ። እነዚህም የብብት ጠረን መከላከያ፣ የአፍ ማጠቢያ፣ ሻምፖዎችን ይጠቀልላሉ።

**ጉርሻ (ቲፕ)** ለምግብ ቤት አስተናጋጅና ለታክሲ ነጂ ካወጡት ወጪ 15-20 በመቶ ጉርሻ ወይንም ቲፕ መስጠት የተለመደ ነው። ከፖሊስ ወይንም ከመንግስት ባለስልጣን ላገኙት አገልግሎት ግን ጉርሻ መስጠት ትክክል አይደለም።

**ሲጋራ ማጨስ** በርካታ አሜሪካውያን ሲጋራ ስለማያጨሱ በቤታቸውም ሆነ በመስሪያ ቤታቸው ሌሎች ሰዎች እንዳያጨሱ ይፈልጋሉ። በአንዳንድ ምግብ ቤቶች ወይንም የገበያ አዳራሾችና ሱቆችን በመሳሰሉ ህዝብ በሚበዛባቸው ቦታዎች፣ ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው ወይንም የሚጨሰው በተለይ በተከለለ ስፍራ ይሆናል።

**የአልኮል መጠጥ** በዩናይትድ ስቴትስ መጠጥ ቢጠጣም ቅሉ ሽያጭና አጠቃቀሙን በተመለከተ በርካታ ህጎችና ደንቦች አሉ። እነዚህ ህጎችና ደንቦች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፣ በአንዳንድ ስፍራዎች ጥብቅ ናቸው። በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ግዛት፣ አልኮል መጠጥ ጠጥቶ መኪና መንዳት ከባድ ወንጀል ነው። ጠጥቶ መንዳት ሊያሳስር፣ በገንዘብ ሊያስቀጣ ወይንም ደግሞ የመንጃ ፈቃድ ሊያስነጥቅ ይችላል። የአልኮል መጠጥ መጠጣት የሚቻልበት እድሜ እንደየቦታው ማለትም 18-21 ዓመት ይለያያል። ከተጠቀሰው እድሜ በታች ያሉ ልጆች አልኮል መጠጣት ብቻ ሳይሆን መግዛትም አይችሉም። በዩናይትድ ስቴትስ መጠጥ ተጋብዘው አልጠጣም ቢሉ፣ ነውር ተደርጎ አይቆጠረም።

**ለደህንነትዎ መጠንቀቅ** በዩናይትድ ስቴትስ ወንጀልና ረብሻ ቢኖርም ቅሉ መጠኑ ከቦታ ቦታ ይለያያል። የትም ሆነ እንዴት ይኑሩ፣ መሰረታዊ የደህንነት ጥንቃቄዎች መውሰድ አለብዎት። ቤትዎንና መኪናዎን መቆለፍ፣ ብዙ ጥሬ ገንዘብ በእጅ አለመያዝና በምሽት መሄድ የማይገባዎት ስፈር የቱ እንደሆነ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል።

**ጠቃሚ መታወቂያዎች መያዝ** I-94ቅጂ ሁል ጊዜ መያዝ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ሁል ጊዜ የማቋቋሚያ ድርጅትዎን ስም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር ይያዙ። እንግሊዘኛ መናገር ካልቻሉ ደግሞ፣ የራስዎን ስልክ ቁጥርና አድራሻ ወይንም ደግሞ የሚጠይቁትን ሰው አድራሻና ስልክ ቁጥር ፅፈው መያዙ ጠቃሚ ነው።

"ለዚች ሀገር የነበረኝ ስሜት ስመጣ ከነበረው በጣም ተለውጧል። ቪየትናም ሳለሁ ወደ አሜሪካ መሄድን ገነት እንደ መግባት አድርጌ እቆጥረው ነበር። ሰዎችም ይህንኑ ነበር የሚሉኝ። ዳሩ ግን አሁን፣ አሜሪካ ከቪየትናም የተሻለች ሀገር እንጂ ገነት አድርጌ አልቆጥራትም።"

"የምንኖረው በአሜሪካ ቢሆንም ቅሉ፣ ባህላችንን የማስታወስና የመጠበቅ መብት አለን። አሁንም ቢሆን የአሜሪካንን ወግና ባህል እየተማርን ነው። አንዳንዶቹን ተቀብለናል። የራሳችን ሀገር እንደሌለን ብናውቅም፣ ባህላችንን በሚገባ እናስታውሳለን እናከብራለን። ወዲህ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የምትመጡ ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ።"

"በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ስለዚች ሀገር ህይወት ሁሉንም ነገር ማወቅ አይቻልም። በርካታ አመታት ይወስዳል።"

"ባለፈው አመት ነው የተለወጥኩት። አሁን አገሬ አይናፍቀኝም። እንደ በፊቱም አዳዲስ ነገሮችን አልፈራም። እንግሊዘኛ ቋንቋን በመማር የተሻለ ስራ ማግኘት እንደምችል ተረዳሁ።"



መልሶ መቋቋም የረጅም ጊዜ ሂደት ነው። የአዲሱን ማህበረሰብ ህይወት በሚገባ ለመልመድ ከሁለት እስከ አምስት አመታት ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ነገሮችን በጥሞና ይከታተሉ፣ ቸኩለው ከድምዳሜ አይድረሱ፣ ለራስዎ ግቦች ይተልሙ። ቅንና ትዕግሰተኛ፣ እርስዎን ሊረዱ ለሚሞክሩ ሰዎች ደግሞ ተባባሪ ሆነው፤ ራስን መቻልና ነፃነት ለሚሉት የአሜሪካ እሴቶች ከበሬታ መስጠትን ቢያክሉበት፣ ራስዎን ለማቋቋም በጣም ይረዳዎታል። ከአዲስ ባህል ጋር መተዋወቅ ጠቃሚና አርኪ እንዲሁም ፈታኝ ሊሆን ይችላል።


Washington
Oregon
California
Idaho
Nevada
Montana
Wyoming
Utah
Arizona
Colorado
New Mexico
North Dakota
South Dakota
Nebraska
Kansas
Oklahoma
Texas
Minnesota
Iowa
Missouri
Arkansas
Louisiana
Wisconsin
Illinois
Michigan
Indiana
Kentucky
Tennessee
Missi-
ssippi
Alabama
Ohio
West
Virginia
Virginia
North Carolina
South
Carolina
Georgia
Florida
Pennsylvania
New York
New Hampshire
Vermont
Maine
Massachusetts
Rhode
Island
Connecticut
New Jersey
Delaware
Maryland
Washington, DC
Alaska
Hawaii
km
400
mi
400
km
700
mi
ALASKA
700
km
400
mi
400

# Continental United States

